# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

# የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ
# የፀደቀ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

## ማውጫ


1. መግቢያ ..... 1
2. የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መነሻዎች ..... 1
3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆዎች እና ዓላማዎች ..... 2
4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና አቅጣጫዎች ..... 4
5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች ..... 24
6. የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን ..... 25
7. የፖሊሲው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ..... 25
8. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች ..... 30
9. መሠረታዊ የቃላት ፍቺ ..... 32

## 1. መግቢያ

የአምራች ኢንዱስትሪ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር መሳለጥ ወሳኝ ሚና ያለው ዘርፍ ሲሆን ባለፉት አመታት ለውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና ለዘላቂ የሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅዖው እያደገ ይገኛል። ይህንን የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ለመምራት የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በ1994 ዓ.ም ተቀርፆ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል። በዚህ ስትራቴጂ እና በሂደት በዳበሩ ሌሎች የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሠረት የተተገበሩ ተከታታይ የልማት ዕቅዶች የአምራች ኢንዱስትሪው በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል።

በተለይም የዘርፉን የግብዓት አቅርቦት በጥራት፣ በብዛትና በአስፈላጊው ጊዜ በሚፈለገው ደረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ የማምረት አቅም አጠቃቀምን የሚወስኑ በርካታ የማይክሮና ማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪው ምርት፣ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት በሚጠበቀው ሁኔታ ማረጋገጥ እንዳይቻል አድርገውታል። በመሆኑም ከዘርፉ የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዳያድግ እንዲሁም ሀገራችን ከውጭ በሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓት እና ፍጆታ ምርቶች ላይ ጥገኛ እንድትሆን አድርጓል። ይህም ለሀገራዊ የንግድ ሚዛን ጉድለት ምክንያት ሆኗል። በሌላ መልኩ በሀገራችን ባለፉት አመታት የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም የሚጠበቀውን የሀገራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት አልተቻለም። የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪው እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በአምራች አንዱስትሪ ልማት ስኬት እንደሆነ ያሳያል።

ስለሆነም በሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ ለማሳደግ እና በሥራ ላይ ባለው ስትራቴጂና ፖሊሲ አቅጣጫዎች ያልተፈቱ ክፍተቶችን ለመሙላት፣ የዘርፉን የመልማት አቅምንና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀም እና ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባህሪያት ጋር የሚመጡ የምርት ስርዓት ለውጥ ለማስተናገድ ይህ አዲስ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል።

## 2. የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መነሻዎች

በ1994 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሲተገበር የቆየው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የግል ባለሃብቱ የኢንዱስትሪ ልማት ሞተር፣ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት፣ ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት እና ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ልማት ዋና ዋና መርሆዎቹ ነበሩ። በተጨማሪም ለአምራቹ የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር አስፈላጊነትን፣ የፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ ባለሀብቱና አርሶ አደሩ፣ በአሰሪና ሠራተኛ መካከል መኖር ስለሚገባው ቅንጅት፣ በአጠቃላይ ስትራቴጂው የሚመራባቸው መርሆች፣ አቅጣጫዎችና የአፈጻጸም ስልቶች ያመላከተ ነበር።

ይህንን ለማጠናከር ከ2007 ጀምሮ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አሰራር ተጨማሪ የመንግስት የፖሊሲ ትኩረት ሆኖ ተተግብሯል። በሌላ መልኩ በቀላል ኢንዱስትሪዎች ላይ አተኩሮ የነበረው የፖሊሲ አቅጣጫ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና መዋቅራዊ ለውጥን በማለም ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ትኩረትን በማስፋት ከባድ የብረታ ብረትና

ኢንጂነሪንግ፣ የኬሚካል እና የፋርማሲዩቲካልስ ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ጅምር ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡

በዚህ ስትራቴጂና በሂደት በዳበሩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሠረት መንግስት በከፍተኛ ወጪ መሠረተ ልማቶች ማስፋፋት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ሼዶች መገንባት፣ በዘርፉ ለተሰማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ፋይናንስና ፋይናንስ-ነክ ያልሆኑ የተለያዩ ማበረታቻዎችን አቅርቧል፡፡

ይሁን እንጂ በዘርፎች መካከል ያለው ትስስር ደካማ መሆን፤ የንዑስ ዘርፎች የአቅርቦት ሰንሰለት በዋናነት በውጭ ጥሬ ዕቃዎች ላይ መመርኮዝ፤ የማበረታቻ ስርዓታት ወጥነት ማጣት እና ከኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም ጋር አለመቆራኘት፤ የኢንዱስትሪ ባህል አለመዳበርና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ዘመናዊ የሥራ አመራርና የጥራት ሥርዓት የተጠናከረ አለመሆን፣ ዝቅተኛ ምርትና ምርታማነት መኖር፤ የምርምር ተቋማት ምርታማነትን ማሳደግ የሚችሉ ዘርፍ ተኮር መፍትሄዎችን ከማመንጨት አንጻር ውስን መሆን፤ ኢንዱስትሪዎች ከዩኒቨርስቲ፣ ከምርምር እና ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር ደካማ መሆን፤ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ቴክኖሎጂን የማሸጋገር ሥራ በሚፈለገው ደረጃ አለመሰራቱ፤ የቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ የመሬት አቅርቦት እጥረት፣ በቂ የሀይል አቅርቦት አለመኖር፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የገበያ ክፍተትን መሰረት ያላደረገ የመንግስት ጣልቃ ገብነት በዘርፉ የተስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ሲሆኑ ይህም በአምራች ዘርፍ ያለውን ዕምቅ አቅም ጥቅም ላይ እንዳይውል አድርጓል፡፡

በመሆኑም ዘርፉ ዘላቂ የስራ ዕድልን ከመፍጠር፣ ውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት፣ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ከመተካት፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ወደ አምራች ዘርፉ ከመሳብ አንጻር የታቀዱ ግቦችን ማሳካት አልተቻለውም፡፡

በአጠቃላይ ዘርፉ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ከማረጋገጥ አንጻር፣ በምርት ሰንሰለቱ ላይ አግባብነት ያለውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የግብዓት ብክነትንና ወጪን ከመቀነስ አኳያ፣ በኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር በማቀላጠፍና በማጥበቅ በምርት ሰንሰለቱ ላይ ምርታማነትን ከጥራት ጋር በማዋሃድ ተወዳዳሪነትን በጠንካራ መሠረት ላይ ከመጣል እና መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣት እንዲሁም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ አሁንም ቢሆን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

በመሆኑም የመንግስት የፖሊሲና የልማት ዕቅዶች ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ትኩረት የሰጠ ሆኖ የሚጠበቀውን ውጤት አለማስመዝገቡ በስራ ላይ ያሉትን የፖሊስ አቅጣጫዎችና የኢንዱስትሪ ስትራቴጂዎችን መፈተሽና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆዎች እና ዓላማዎች

### 3.1 የፖሊሲው አስፈላጊነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማውጣት ያስፈለገበት መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘርፉን ለመምራት በ1994 ዓ.ም ተቀርፆ ሥራ ላይ በዋለው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የታዩ የፖሊስ አቅጣጫዎች አፈፃፀም ክፍተቶችን ለማስተካከልና መፍትሔ ለማስገኘት እንዲሁም ጊዜውን የዋጀ የፖሊሲ መርህና አቅጣጫ ለውጥና ማሻሻያ ለማድረግ፣

- በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (homegrown economic reform) የተቀመጡትን የፖሊስ አቅጣጫዎች አጣጥሞ ለመምራት፣ ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባህሪያት ጋር የሚመጡ የምርት ስርዓት ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲሁም የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎችና የመልማት አቅም በስፋት በመጠቀም በምርት ብልጫ እና የተወዳዳሪነት ጽንሰ ሐሳብ/ፍልስፍና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ፣

- በወጪ ንግድ ላይ ብቻ አትኩሮ የነበረውን ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካትን ባጣጣመ መልኩ ለመምራት፤ የግል ባለሀብቱን በአምራች ኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ የማበረታቻና ብድር አቅርቦትን ውጤታማነት ለማሳደግ፤ የአካባቢና የተፈጥሮ ሃብትን መሠረት ያደረገ ተመራጭና ተወዳዳሪ ምርት ማምረትን የተከተለ የኢንዱስትሪ ክላስተር (አንከር ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት) አሰራር መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣

- የአምራች ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስርና ቅንጅት ለማሳደግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሌሎች የዘርፍና የማክሮ ፖሊሲዎች ጋር በማስተሳሰር የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ በማስፈለጉ፣

- ግልጽና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ በቂ የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን (ፖሊሲውን የሚያስፈጽም ተቋማዊ አደረጃጀትና ሃላፊነት፣ የህግ ማቀፎችና አሰራሮችን፣ የልማት ፕሮግራሞችን እና የክትትልና ግምገማ ስርዓት) በመለየት በፖሊሲው ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ፣

- ሀገሪቱ ያላትን ዕምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ወጥና ሁሉን አቀፍ የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ይህ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል።

### 3.1. የፖሊሲው መርሆዎች

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲዉን ውጤታማ ለማድረግ በሚከተሉት መርሆዎች መሠረት የሚመራ ይሆናል።

- **ገበያ መር፦** የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የገበያ መር አቅጣጫ ይከተላል።

- **በግሉ ዘርፍ የሚመራ፦** የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ መሪ ተዋናይ ይሆናል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሀገር ውስጥ አምራቾችን የሚያሳድግ፣ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሃብትን አቀናጅቶ መጠቀም እና የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት አቅጣጫ ይከተላል።

- **ግልፅ የመንግስት ሚና፦** መንግስት ምቹ የአምራች ኢንዱስትሪ ስነ-ምህዳር መፍጠር በተለይም የተቀናጀና የተናበበ የመንግስት አገልግሎት ማቅረብ ዋነኛ ሚናው ሲሆን በግሉ ዘርፍ ሊተገበሩ የማይችሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም በግሉ ዘርፍ መተግበር የሚገባቸው ሆኖም ግን የግሉ ዘርፍ ያልተሳተፈባቸው ስትራቴጂክ ተብለው በሚለዩ ምርቶች ላይ አዋጪነቱን በጠበቀ መንገድ እንደ አምራች የገበያ ጉድለቱን ለመሙላት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ወይም በተናጥል ይሳተፋል፤ የግሉ ዘርፍ እና የገበያ አቅም ሲዳበር በሂደት ይወጣል።

- **የኢንዱስትሪ ክላስተር፦** የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የተቀናጀ ግብዓት፣ ምርትና አገልግሎትን መሠረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ክላስተር ይከተላል፣ ይህም የአካባቢ የተፈጥሮ ፀጋን ያገናዘበ፣ የከተማና ገጠር ትስስርን የሚያጠናክር እና ከአካባቢ ልማት ዕቅድ ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲመራ ይደረጋል።

- **ለወጪና ተኪ ምርት የተመጣጠነ ትኩረት የሰጠ፦** የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች አንጻራዊ የምርት ብልጫ እና ተወዳዳሪነትን መሰረት በማድረግ ለውጪ ገበያ በማቅረብና ከውጪ የሚገቡ ስትራቴጂክ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የንግድ ሚዛንን በጠበቀ መልኩ ይመራል።

- **አካታችና ዘላቂ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት፦** የፖሊሲው ትግበራ አካታችና ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ያረጋግጣል።

- **የተጣጣመ የሕግ ማዕቀፍ፦** ሀገራችን አባል የሆነችባቸውን የአካባቢያዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይፈፀማል።

### 3.2. የፖሊሲው ዓላማዎች

የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ዋናው የፖሊሲው አላማ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም ይኖሩታል፦

- ለአምራች ኢንዱስትሪ ምቹ ሥነ-ምኅዳር መፍጠር፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ኢንቨስመንት መጠን ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ሃይል ምርታማነት ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ወደ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የምርት ስርዓት ማሻገር፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም፣ እሴት ጭመራ እና ጥራት ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪውን የአካባቢ እና ማኅበራዊ አካታችነትና ዘላቂነት ማሳደግ፣ ናቸው።

## 4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና አቅጣጫዎች

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ርዕይ፣ ግብና ዓላማ ለማሳካት በስራ ላይ ያሉትን የስትራቴጂና የፖሊስ አቅጣጫዎችና መርሆዎች መሰረታዊ ለውጦች ለማምጣት እንዲሁም ለማስፋትና ለማጠናከር እንዲያስችል ስድስት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ተነድፈዋል። እነዚህም ማክሮ

ኢኮኖሚና የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር፣ ፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት፣ የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ የምርት ልማትና ተወዳዳሪነት እና አካታችነትና ዘላቂነት ናቸው።

## 4.1 ምርት ልማትና ተወዳዳሪነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት ተወዳዳሪነት ማሳደግ የኢንዱስትሪ ልማት ዋና አቅጣጫ ሲሆን ይህንን አቅም በመፍጠርም ምርቱ በሀገርና በዓለምአቀፍ ገበያ ውስጥ በዘላቂነት የመቆየት አቅሙ እንዲዳብር ያደርገዋል። በመሆኑም የሀገራችን ኢንዱስትሪ ልማት ምርትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር የተከተለ፣ በተጠናከረ የግብዓት ምርት ልማት ትስስር የሚደገፍ ፣ ለወጪ ንግድና ለተኪ ምርት ልማትና ግብይት እንዲሁም ለምርት ጥራት ሥራ አመራር ትኩረት የሚሰጥ ሆኖ መመራት ይኖርበታል።

### 4.1.1 ምርትን መሠረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር መዘርጋት

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት መሠረት አድርጎ በተቀራራቢ አካባቢ በማሰባሰብ ማልማት የግብዓት ምርት ትስስር ለመፍጠር፣ የሰው ኃይል ለመጠቀም፣ ለገበያ ተደራሽ ለመሆን እንዲሁም የቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ለማሳለጥ ይረዳል። በተዘረጉ ኢንዱስትሪ ዞን፣ የኢንዱስትሪ መንደር፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የተቀናጀ የአግሮአንዱስትሪ ፓርክ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ሼድ ግንባታዎች ውስጥ እና ከዚያ ውጭም ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚመጋገቡበትና የሚተሳሰሩበት አሠራርና ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ አልተዘረጋም። የግብዓትና ምርት ግብይት ስርዓቱን ተከትለው በተፈጥሮ የመልማት ፀጋ ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ልማት በተለይም በኢንዱስትሪ ክላስተር የተሰባሰቡ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚደገፉበት አሠራርና ሥርዓት አልተዘረጋም። የአምራች ኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት በገቢ ንግድ ላይ እንዲንጠለጠል በማድረጉ የኢንዱስትሪዎች የእሴት ጭመራን ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል። በተመሳሳይም የኦርጋኒክ ክላስተሮች አልተስፋፉም፣ ይህም ወደ ተመራጭ ኢንዱስትሪ ልማት አላሸጋገረም። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በኢንዱስትሪ ክላስተር አሠራር ሥርዓት እንዲመራ ይደረጋል። ይህም ከኢንዱስትሪ ማፐ ጋር የተናበበ ሆኖ ይመራል።
- የአምራች ኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት መሠረት ያደረገ ስትራቴጂክ ምርት ተኮር እንዲሆን ይደረጋል። ምርቱም መሪና የተመራጭ (Anchor) ኢንዱስትሪዎችን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን እንዲያገናዝብ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ክላስተር አሠራር ሥርዓት የተፈጥሮ ክላስተሮች የሚያሳድግና የሚያሳትፍ ሆኖ እንዲመራ ይደረጋል።

### 4.1.2 የአምራች ኢንዱስትሪ የግብዓት ምርት ትስስር ማረጋገጥ

ተወዳዳሪ የአምራች ኢንዱስትሪ ለመገንባት በሀገር ውስጥ ግብዓት ልማትና አቅርቦት ጋር የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጾ ያበረክታል። ይህም እሴት ሰንሰለትን መሠረት ያደረጉ የመጀመሪያ ደረጃ ምርት ልማት፣ በተለይም የግብርናና የማዕድን እንዲሁም ተመጋጋቢ አምራች ኢንዱስትሪዎች ልማት እንዲስፋፉ ለማድረግ አሰራሮችን በመቀየስና የማበረታቻ

ሥልቶችን በመንደፍ የግብዓት ምርት ልማትና ኢንዱስትሪ ትስስር ማሳደግ  እጅግ በጣም መሠረታዊ ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡

ሆኖም ግን የአምራች ኢንዱስትሪ እና የግብዓት ምርት አቅርቦት ልማትና ትስስር የተሟላ የድጋፍና የማበረታቻ አሠራርና ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በተለይም የግብርና ምርት እድገት ለአምራች ኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎት መሠረት አድርጎ  የተመራ ያልነበረ በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኮንትራት ፋርሚንግ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የአሰራር ስርዓት እንዲዘጋጅ ሆኗል፡፡ በዚሁ አግባብ ግን ስርዓቱን በተሟላ ሁኔታ ወደ ተግባር የመለወጥ ስራዎች ይቀሩታል፡፡ በተመሳሳይ ለአምራች ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት ማልማትና ማበልፀግ የሚችል የተሟላ የአሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በሌላ መልኩ በአምራች ኢንዱስትሪው መካከል እሴት የተጨመረበትን ምርት ግብዓት ልማትና ትስስር አሠራር ሥርዓት በሚገባው ደረጃ አልዳበረም፡፡ በዚህም ለአምራች ኢንዱስትሪው በቂ የሀገር ውስጥ ግብዓት ማቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት ዝቅተኛ የማምረት አቅም አጠቃቀም እና ከውጪ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ መሆን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ወጪ አስከትሏል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ በእያንዳንዱ የእሴት ሰንሰለት ከሚፈለጉ የምርት ግብዓቶች (የሰው ኃይል፣ ጥሬዕቃ፣ ቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት ወዘተ) ከሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ እንዲጠቀሙ ለማስቻል ወይም ለማረጋገጥ በቅድሚያ የተወሰነ የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ እና የማበረታቻ አሰራር በተሟላ የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ ስርዓት ባለመመራቱ የአገር ውስጥ ግብዓትን የመጠቀም አቅምን ለማነቃቃት እና የአቅርቦትን ጥራት ለማሻሻል አልተቻለም፡፡ ምርታቸውን ለወጪ ንግድ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት የሚተኩ አምራቾች  የገዢዎቻቸውን ፍላጎት በማሟላት በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከላይ የቀረቡትን የፖሊሲ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት፣

- በአምራች ኢንዱስትሪውና የመጀመሪያ ደረጃ ግብዓት አቅራቢ ዘርፎች (በተለይም ግብርናና ማዕድን) የግብዓት ምርት ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ድጋፍና የማበረታቻ አሠራርና ሥርዓት (የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 መተግበርን ጨምሮ) እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

- በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የግብዓት ምርት ትስስር ለማጠናከር የሚያስችሉ የድጋፍና የማበረታቻ አሠራርና ሥርዓት (የታሪፍ ከለላዎች ማሻሻያን ጨምሮ) እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

- የአምራች አንዱስትሪ የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ (local content) የተዘዋዋሪ የወጪ ንግድን (deemed export) በሚያበረታታ መልኩ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ይህም በምርት መሠረት ያደረገ ከኢንዱስትሪ ክላስተር አሠራር ጋር ይቀናጃል፣ ውጤታማና ተጠያቂነት የሰፈነበት የግብዓት ምርት ትስስር አሠራርና ሥርዓት እና የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይጠናከራል፡፡

### 4.1.3 የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪው የወጪ ንግድ አመቺ የሆነ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና ከቀረጥና ኮታ ነጻ የገበያ ዕድሎች አሟጦ በመጠቀም በግብርና ላይ ተንጠልጥሎ የሚገኘውን የሀገራዊ የውጭ

ምንዛሬ ግኝት ድርሻ ለማሳደግ እንዲሁም ያለማቋረጥ ተወዳዳሪነትና ምርታማነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና አለው፡፡

ሆኖም ግን የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ እና ትኩረት ያደረገ የተሟላ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ አሠራር ሥርዓት፣ በተለይም ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው ተቋማዊ ቅንጅታዊ አሠራር አለመዘርጋቱ እንዲሁም የወጪ ንግድ ማስፋፊያና ማበረታቻ ሥርዓቶች ምርታማነት፣ ጥራትና ተወዳሪነትን በተሟላ መልኩ መደገፍ አልቻለም፡፡ ይህም አምራች ኢንዱስትሪው ዝቅተኛ የወጪ ንግድ አፈፃፀም እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ አቅም ለመፍጠር በሚያግዝ መልኩ አምራቾቹ ያመረቷቸውን ምርቶች በማሰባሰብ ወደ ውጪ የሚልኩበት የአሠራር ሥርዓት፣ በገበያ የተመራ የአምራች የወጪ ንግድ ኮንሶርቲየም ማቋቋምን ጨምሮ እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ የአሠራር ሥርዓት፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር ጨምሮ እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ የጎረቤትና አህጉራዊ አገሮችን የምርት እሴት ሰንሰለት መሠረት ያደረገ የዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብት አስቻይ ሁኔታዎች እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

### 4.1.4 ከውጪ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት

የተለያዩ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪ መሰረትን ለማስፋት፣ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በጥራትና ተወዳዳሪነት ለማሟላት ብሎም በዘላቂነት ምርቱን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ጠንካራና ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ መገንባት የቻሉት ገቢ ምርት የሚተኩ ኢንዱስትሪ ላይ አትኩረው በሠሩት ሥራ ነው፡፡ የውጪ ንግድ ከማስፋፋት ጎን ለጎን በተመረጡ ምርቶች ላይ ባተኮረና አዋጭ በሆነ መልኩ በቂ አቅም ባለባቸው ቦታዎች የተኪ ምርት ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል፡፡ ይህም ለወጪ ንግድ ምርት ግብዓት የሚያገለግሉ እና ከፍተኛ የተኪ ምርት አቅም ያላቸው የመጨረሻ ምርቶችን ያካተተ ነው፡፡

ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ጀምሮ የመንግሥት የፖሊስ አቅጣጫ ሆኖ የተቀመጠ ቢሆንም የተኪ ምርት አቅም ያላቸውን ምርቶችና ግብዓቶች የሚሠሩ አምራቾችን የሚደግፍ የተሟላ የድጋፍና የማበረታቻ አሠራርና ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በተለይም የሀገር ውስጥ አምራቾች ከውጪ የሚገቡ በከፊል የተጠናቀቁ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ያለቀለት ምርት ለማምረት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በግብዓቶቹ ላይ የተጠናቀቁ ምርቶች ላይ ተደራራቢ ታክስና ቀረጥ በበለጠ ምጣኔ እንዲከፈልባቸው መደረጉ የፖሊሲው ክፍተት ማሳያዎች ናቸው፡፡ ይህም ለከፍተኛ የገቢ ምርት ጥገኛ ኢኮኖሚ እንዲፈጠርና ሀገራዊ ንግድ ሚዛን መዛባት አስከትሏል፡፡ በተጨማሪም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚመረቱ ምርቶች ከውጪ በህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መልኩ የሚገቡ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ጋር መወዳደር እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- ከውጪ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ የተመረጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት አስፈላጊውን ድጋፍና ማበረታቻ በማድረግ የምርት ተወዳዳሪነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

- ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ህጋዊነት እና የታሪፍ ከለላዎች እንዲሁም የምርት ግብይት ስራት እንዲጠናከር ይደረጋል ፡፡

- የሀገር ውስጥ ምርት ማስተዋወቅና ማስፋፋት ሥራዎች ተጠናክረው ይሰራሉ፡፡

### 4.1.5 የአምራች ኢንዱስትሪ የምርት ጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ማጠናከር

የአምራች ኢንዱስትሪው በተለይም በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ገበያው የሚፈልገውን ደረጃ ለማሟላት የምርት ጥራቱን በዘላቂነት ማሻሻል ይፈልጋል፡፡ በተመሳሳይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ለማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች የሚፈለገውን የጥራት ደረጃን እንዲያሟሉ እና ተገቢ ዋጋ እንዲኖራቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ግን የአምራች አንዱስትሪ ምርት ጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት የተሟላ የማበረታቻና የማስፈፀሚያ አሠራር አልተዘረጋም፡፡ ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- የአምራች አንዱስትሪ ምርት ጥራት ሥራ አመራር ስርዓት የሚደግፍና የሚያበረታታ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

- የምርት ጥራት ስራ አመራር ተግባራዊ ለማድረግ ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሠራር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## 4.2 የሰው ኃይል ልማት እና አስተዳዳር

በኢንዱስትሪ ባህል እና በሥራ አመራር ክህሎት የዳበረ የሰው ኃይል ማቅረብ እንዲሁም የቀረበውን የሰው ኃይል መቅጠርና ምርታማነትን ማሳደግ ያካትታል፡፡

### 4.2.1 የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ልማትና ክህሎት ማሳደግ

የሰው ኃይል ልማት ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አንፃር የተዘጋጀ ዕውቀትና ክህሎት፣ የኢንተርፕርነርሺፕ ክህሎት እና የኢንዱስትሪ ባህልን የተላበሰ ሠራተኛ እንዲሁም በሥራ አመራር ብቃት የተገነባ የኢንዱስትሪ አመራር ለዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት የሚጫወተው ሚና ጉልህ ነው፡፡ በሀገራችን የቴክኒክ ክህሎትና የክህሎት-ልቦና ሥልጠና አግኝቶ በአምራች ኢንዱስትሪዎች ለመቀጠር ዝግጁ የሆኑ በቀላሉ ሊሠለጥኑ የሚችሉ ወጣቶች አሉ፡፡

ሆኖም ግን የትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፎች ጥራት ያለው የሰው ኃይል ማብቃትን የሚከታተልበት አሠራር በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም፡፡ በመሆኑም የሚቀረጹ የትምህርት ካሪኩለሞች የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጎት በሚገባ ያላገናዘቡና የኢንዱስትሪ ባህል መፍጠርን ጨምሮ በተግባር የተደገፈ እንዲሁም የሥራ ፈጠራ(ኢንተርፕረነርሺፕ) ክህሎትን የፈጠረ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም የኢንዱስትሪ እና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስር የማበረታቻ፣ የባለቤት እና የተጠያቂነት ማዕቀፍ አለመዘርጋት ዋና ዋና ክፍተቶች ሆነው ተስተውለዋል፡፡ በተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስልቶች ክህሎትን በሚያሳድግ መልኩ የተጠናከረ የማስተግበሪያ አሠራር አልተዘረጋም፡፡ ይህም የቴክኖሎጂ ሽግግሩን አዝጋሚ

አድርጎታል፤ አምራቹን ለከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ወጪ ዳርጎታል። በሌላ መልኩ ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ክህሎቶች በተለይም በልምድ የዳበሩ ክህሎቶችን ደረጃና ዕውቅና የሚያረጋግጥ ሥርዓት በሀገራዊ የክህሎት ማረጋገጫ ውስጥ አልተካተተም። በዚህም ከአምራች ኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር የተስማማ በቂ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማቅረብ አልተቻለም። በአጠቃላይ የሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ምርታማነት አልተሻሻለም። በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

- የአምራች ኢንዱስትሪ እና የከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ትስስር የሀገራዊ የተቋማት ትስስር የሕግ ማዕቀፍ በመመርኮዝ የማስፈፀሚያ መመሪያና ሥርዓት (ኢንተርንሺፕ፤ አፓረንትሺፕ፤ ኤክስተርንሽፕ፣ ሴት ሠልጣኝና ምሩቃን ማብቃት እና ክህሎትና ዕውቀት ያዳበሩ አምራቾች በከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት የሚያስተምሩብት ሥርዓትን ጨምሮ) ይነደፋል፣ የማበረታቻና የተጠያቂነት አሰራር ይዘረጋል፣

- በከፍተኛ ትምህርት እና የስልጠና ተቋማት፤ በኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከላት እና በአምራች ኢንዱስትሪ በጋራ የሚቀረጹ ካሪኩለሞች የአምራች ኢንዱስትሪ ፍላጎትን (ጥራትና መጠን) የሚያሟላ እና የኢንዱስትሪ ባህልን የሚያዳብር እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ስርዓቶች ክህሎትን በሚያዳብር መልኩ እንዲጠናከር ይደረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪውን የማኔጅመንትና ቴክኒካል ፍላጎቶች መሰረት ያደረገ የክህሎት ልማት ለተለዩ ዘርፎች እንዲከናወን ይደረጋል፣ አመራሩ በእውቀትና ክህሎት እንዲመራ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

### 4.2.2 የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል አስተዳደርና ምርታማነት ማሻሻል

የአምራች ኢንዱስትሪ መስፋፋት የሥራ ዕድል አማራጮችን በማሳደግ በፋብሪካዎች ውስጥ መሥራት በሂደት የፋብሪካ አመራር እና ባለቤት የመሆን እድልን የሚያጎናጽፍ ከመሆኑ አኳያ ከሌሎች አማራጭ ሥራዎች የበለጠ ተመራጭ እንደሚያደርገው ይጠበቃል። መንግስት ሠራተኛውና አሰሪው ለኢንዱስትሪ ልማት መፋጠንና በየደረጃቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በጋራና በቅንጅት እንዲረባረቡ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ የአመራር ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ሆኖም ግን በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት ያለውን እድልና ስጋት ከሌሎች ሥራዎች ሠራተኛ ለመሳብ የሚያስፈልጉ የሥልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ አሠራርና ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ አልተዘረጋም። በሌላ መልኩ በስራ ላይ ያለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል ለመሳብ፣ ለማቆየትና ምርታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለማስፈፀም ክፍተት ይታይበታል። ምርታማነትን የማሻሻል ሥራ በዋናነት በመንግሥት ይሰራ የነበረ መሆኑ በተለይም የግል ዘርፉና የመንግሥት ቅንጅትን ባጠናከረ መልኩ አልተመራም። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ምርታማነት አነስተኛ እንዲሆን አንዱ ምክንያት ሆኗል። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

➢ የአምራች ኢንዱስትሪ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ምርታማነት በሚያሳድግ መልኩ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

➢ የአምራች ኢንዱስትሪው ሠራተኛ የሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት በጠበቀ መልኩ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

➢ የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት፣ አሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሥርዓት ይዘጋጃል፡፡ ይህም የአሰሪውና የሠራተኛውን መብትና ግዴታ ባገናዘበ ሁኔታ የሰው ኃይል ምርታማነት በሚያበረታታ መልኩ ይሆናል፡፡

➢ የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል የሰው ሃይሉን ውጤታማ የሚያደርጉ የጥራትና የምርት አመራር ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 4.3 የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን አቅም

ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንዲሁም ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የምርት ሥርዓት ለማሻገር ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን አቅም የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም በማሻሻል ቴክኖሎጂ መፍጠር፣ ማልማት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ከማስቻሉም በላይ በተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ሽግግርን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ በማሳደግ ረገድ ከፈተኛ ፋይዳ አለው፡፡

### 4.3.1 የአምራች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት አቅም ማሳደግ

ለሀገራችን ቴክኖሎጂ መቅዳትና ማላመድ፣ ማሻሻል፣ ማበልፀግ፣ መፍጠርና ማልማት እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም የሚቻለው የተጠናከረ የምርምር ሥርዓት እና የሚመለከታቸው ተዋንያን የሚጠበቅባቸውን ሚና ሲጫወቱ ነው፡፡ ሆኖም እስካሁን ያለው አፈጻጸም ሲታይ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት የሚደገፍበትና የሚመራበት የተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት ካለመዘርጋቱም በተጨማሪ የምርምር ባህል የሚዳብርበትና የሚበረታታበት የአሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪን ያማከለ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ የሚደገፍበትና የሚመራበት እንዲሁም የግል ዘርፉ በምርምርና ልማት ተሳትፎ የሚያሳድጉ የተሟላ የአሠራር ሥርዓቶች አልተዘረጉም፡፡ የአምሯዊ ንብረት ጥበቃ፣ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ የሚመራበት የተሟላ አሠራርና ሥርዓት አልተጠናከረም፡፡ ይህም ለአምራች ኢንዱስትሪው በቂና የተሟላ የሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂ እንዳይቀርብና አዳዲስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንዳይስፋፋ ሆኗል፡፡በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

➢ የአምራች ኢንዱስትሪ የምርምርና ልማት ሥርዓት ሁሉን ተዋንያን አሳታፊ ባደረገ የግሉን ምርምር ተሳትፎና ውጤታማነት እንዲያሳድግ ይደረጋል፣ የምርምርና ልማት ተቋማት ውጤታማነትና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

➢ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ገበያ፣ ምርትና አገልግሎት የሚሸጋገሩበት የቴክኖሎጂ ኮሜርሻላይዜሽን አሰራር ይጠናከራል፡፡

- የአምራች አንዲስትሪው በሀገር ውስጥ የሚለሙ ምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪው ከምርምር፣ የከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር የምርምርና ልማት ሥራዎችን በአጋርነት የሚያካሂዱበት አሰራር ይጠናከራል፣ ይደገፋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪን ያማከለ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

- የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል።

### 4.3.2 የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪው በዓለማቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከሚያስችሉት ጉዳዮች አንዱ ተስማሚ የሆነ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ማመቻቸት እና ተጠቃሚ ማድረግ ነው። የሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት የሚጠይቀው የቴክኖሎጂ ግብዓት በተለይ ኢንዱስትሪው በማቆጥቆጥ ላይ ያለና ጀማሪ በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ነው።

በነባሩ ፖሊሲና የማስፈጸሚያ አሠራር ሥርዓቱ ላይ የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የቴክኖሎጂ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራርን ጨምሮ የሚደገፍበትና የሚመራበት የተሟላ አሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም። የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂን ከውጪ ለማስገባትና ለመጠቀም በተሟላ አሠራር ሥርዓት አልተጠናከረም። የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለማሻሻል እና ለመደገፍ የሚያስችል አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ አልዋለም። ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂ እና ጉልበት አጠቃቀም የሚኖረውን መስተጋብር የሚመራበት አሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም። በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪ በቂና የተሟላ ቴክኖሎጂ አልቀረበም፣ የቴክኖሎጂ ሽግግሩም በሚፈለገው ልክ አልተጓዘም። እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ይሻሻላል፣ ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመጠቀም፣ ለማሻሻል፣ ለመፍጠር እንዲሁም ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማና ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር በሽግግር ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ዋጋና የአገልግሎት ጊዜን ለመገመት የሚያስችል ሥራ እንዲሰራ ድጋፍ ያደርጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይጠናከራል፣ የቴክኖሎጂ ተቋማት ውጤታማነትና ቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፓርኮች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ መረጃና እውቀት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.3.3 የአምራች ኢንዱስትሪ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል የቴክኖሎጂ ዕድገትና አጠቃቀምን ለማሳደግ ዘመናዊ የሆኑ የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን የአምራች ኢንዱስትሪ በዓለም ገበያ ውስጥ በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ ለመሆን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታና የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም፡፡ በዚህም ምክንያት የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጦታል፡፡ ይህም የምርት ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በሌላ መልኩ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ላደጉም ይሁን በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት እኩል ዕድል የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በስፋት ይታያል፡፡ እነዚህም ባዮ ቴክኖሎጂ፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ ማቴሪያል ሳይንስ እንዲሁም ሰው ሰራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንቴለጀንስ) እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በሀገራችን በዚህ ዘርፍ ብዙ አቅም ቢኖርም በአግባቡ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- በተመረጡ አምራች ኢንዱስትሪ የሶስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ላይ በመመርኮዝ ወደ አራተኛ የኢንዱስትሪ አብዮት እንዲሻገር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን እና ኢመርጀንግ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፡፡
- ከሀገራዊ የአርተፊሻል ኢንተሊጀንስ የፖሊስ ማእቀፍ ጋር የተጣጣመ እና ለሰው ኃይል አጠቃቀምና ማህበራዊ አካታችነት ትኩረት እንዲያደረግ ይደረጋል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን አጠቃቀምና አስተዳደር የማበረታቻና ድጋፍ አሠራርና ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪ የኢመርጀንግ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር የማበረታቻና ድጋፍ አሠራርና ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 4.4 የፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት

ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂና ውጤታማ ፋይናንስ ለማቅረብ የተጠናከረ የብድር አቅርቦት፣ የውጪ ምንዛሪ ፣ የመድን ሽፋን እና ባንክ-ነክ ያልሆኑ ሌሎች የፋይናንስ ምንጮችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### 4.4.1 ለአምራች ኢንዱስትሪ የብድር አቅርቦት ማሳደግ

ለአምራች ኢንዱስትሪ የረዥም ጊዜ የፕሮጀክት እና የሥራ ማስኬጃ ብድር በበቂ መጠንና ዋጋ በቀልጣፋና ግልፅ የሆነ አሠራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ግን የልማት ባንክ ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂ የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት እና የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ብድር ለማቅረብ ከንግድ ባንኮች ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ አሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ የብድር አቅርቦት ሂደቱ ረጅም፣ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ እና ግልፅነት የሚጎለው በመሆኑ የተሳለጠ አገልግሎት ማቅረብ አልተቻለም፡፡ የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትል አሠራር ሥርዓት ውጤታማ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም የልማት ባንክ ለጥቃቅንና አነስተኛ አምራቾች

የሚያቀርበው የሊዝ ማሽን የፋይናንስ የተንዛዛ ሂደትና የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች የታለመለትን ዓላማ ግብ እንዳይመታ የሚያደርግ ነው፡፡ የንግድ ባንኮች የአምራች ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት ብድር በሰፊው ለማቅረብ የብድር ድርሻ በህግ ገደብ ታጥሯል፡፡ የንግድ ባንኮች ለአምራች ኢንዱስትሪው የሥራ ማስኬጃ ብድር ከማቅረብ ይልቅ የአጭር ጊዜ ትርፍ ወደ ሚያስገኙ እና ስጋታቸው ዝቅተኛ ወደሆነ እንደ ንግድ ዓይነት ዘርፎች ላይ ማተኮራቸው ለዘርፉ በቂ የሥራ ማስኬጃ ብድር እንዳይኖር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከሚሰጡት ብድር አንፃር ከፍተኛ የሆነ የብድር መያዣ ዋስትና ይጠይቃሉ፡፡ በዚህም የባንክ ዘርፉ ከአምራች ኢንዱስትሪው ፍላጎት አንፃር በቂና ውጤታማ ብድር ማቅረብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም እነዚህን የፖሊሲ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት፣

- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር አቅርቦት ለማሻሻል የፖሊሲ ባንክና ንግድ ባንኮች ዘርፉ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋፅኦ አንፃር የሚያበረታታ የብድር ድርሻ እንዲያድግ እና የብድር አይነቶች እንዲሰፉ ይደረጋል፡፡

- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር አቅርቦት የብድር ዋስትና ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶችን እንዲያካትት ይደረጋል፡፡

- ባንኮች የአምራች ኢንዱስትሪውን ሊደግፍ የሚችል የብድር እና የፋይናንስ የአሰራር ስርዓት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

- ራሱን የቻለና የፖሊስ ተግባር የሚወጣ የአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ ይቋቋማል፡፡

### 4.4.2 ለአምራች ኢንዱስትሪ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪው ለማምረቻ መሳሪያና መለዋወጫ እና ግብዓት የውጪ ግዢ ለመፈጸም የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ ዘርፍ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የወጪ ንግድን ለማበረታታት የሚወጡ የውጪ ምንዛሪ አሠራሮች የውጭ ምንዛሬ አስተዳደሩ የአምራች ኢንዱስትሪውን ልዩ ባህሪ ያላገነዘቡ መሆን ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂና የተሟላ የውጪ ምንዛሪ ማቅረብ እንዳይቻል አድርጓል፡፡ በተለይም የአምራች አንዱስትሪ ግብዓት አስመጪዎች የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት እጥረትን ለመቅረፍ የተከተሉት መንገድ የሀገር ውስጥ ምርቶችን በተለይም የግብርና ምርቶች በከፍተኛ ዋጋ በመሰብሰብ ለወጪ ንግድ በአነስተኛ ዋጋ ወይም በኪሳራ ማቅረብ የተከተለ ሲሆን ይህንን ለማካካስ ከውጪ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ዋጋ ላይ በመጫን ለአምራች ኢንዱስትሪው ፈታኝ ሆኗል፡፡ ከወጪ ንግድ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ የአምራች ኢንዱስትሪ የውጪ ንግድ ምርቶች ለማምረት የሚያግዙ ግብዓቶችን ለማስገባት ከመጠቀም ይልቅ ከፍተኛ የትርፍ ህዳግ ላላቸው የአገለግሎትና የቅንጦት ቁሳቁሶችን ከውጪ ለማስገባት በመዋሉ የአምራች ኢንዱስትሪውን በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳው ይገኛል፡፡ በሌላ መልኩ የባንኮች የውጪ ምንዛሪ አቅርቦትና አጠቃቀም መከታተያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ እንዲሁም ኢንዱስትሪውን ከፊት አድርጎ የንግድ ቢዝነሳቸውን እንዳይደጉሙ የሚያደርግ የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በዚህም ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂና የተሟላ የውጪ ምንዛሪ ማቅረብ እንዳይቻል አድርጓል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል፤

- የአምራች ኢንዱስትሪውን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት አሠራር ሥርዓት እንዲሻሻል ይደረጋል።

- አምራች ኢንዱስትሪዎች ከወጪ ንግድ የሚያስገኙትን የውጭ ምንዛሬ ለራሳቸው የሚጠቀሙበት ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡት የግብዓት መጠን እና የሚያስፈልጋቸውን የካፒታል እቃዎች ፋይናንስ ለማድረግ በሚያስችል መልክ እንዲጣጣም ይደረጋል።

- ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚቀርበው የውጪ ምንዛሬ ኢንዱስትሪው ከሚያስገኘው ወይም ከሚያድነው የውጪ ምንዛሪ መጠን አንፃር መከታተያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይህም ከውጤት ተኮር ማበረታቻ ሥርዓት ጋር የተናበበ ይሆናል።

- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

### 4.4.3 ለአምራች ኢንዱስትሪ የመድን ሽፋን ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪው በአመራረቱ ቀልጣፋ፣ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ ለመቀጠል በማምረቻ ፋሲሊቲዎቻቸው በሚፈጠሩ ችግሮች፣ የማምረቻ መሳሪያ ብልሽት፣ የምርት ስርጭት፣ የሠራተኛ ደህንነት፣ የፖለቲካና የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች በስጋት የታጠረ ነው። ለዚህም አስተማማኝ የመድን ሽፋን ይፈልጋል።

በዚህም መንግሥት በኢንዱስትሪ ፖሊሲው የአምራቹና ሠራተኛ ማህበራዊና ደህንነት ለማረጋገጥ የኢንሹራንስና ጡረታ አገልግሎት ማስፋፋት፣ ከኢንሹራንስና ጡረታ አገልግሎት የሚገኘውን ቁጠባ ለኢንቨስመንት ፋይናንስ የሚውልበትን ቀልጣፋ ሥርዓት መንግሥት መፍጠር እንደሚኖርበት ያስቀመጠ ቢሆንም ለአምራች ኢንዱስትሪው የተሟላ የኢንሹራንስ ሽፋን የሚያገኝበት አሠራር አልተዘረጋም። በተጨማሪም ለአምራች ኢንዱስትሪው ከግጭት ጋራ የተያያዙ ጉዳቶችን ማካካሻ ክፍያ ተገዳሮቶች ይታያሉ። ይህም የኢንቨስተመንት ፍሰቱን ይገድባል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚወሰዱ ይሆናል።

- የኢንሹራንስ ተቋማት ለአምራች ኢንዱስትሪው የተሟላ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያቀርቡ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

### 4.4.4 ለአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ-ነክ ያልሆኑ ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት ማሳደግ

ከመደበኛው የባንክ ብድር አገልግሎት አሰጣጥ ውጭ ያሉ ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት አይነቶች ማስፋት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በተሻለ ሁኔታ በፋይናንስ ለመደገፍ ትልቅ አማራጭ የሚፈጥር ነው። በሀገራችን የፋይናንስ አቅርቦት በአብዛኛው የተንጠለጠለው በባንክ ዘርፍ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪው በአማራጭ ሊጠቀምበት የሚያስችል ሌሎች ባንክ-ነክ ያለሆኑ የፋይናንስ አቅርቦት አልተስፋፋም። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚወሰዱ ይሆናል።

- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት በተለይም የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ከካፒታል ገበያ እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ለመተግበር የሼር ገበያ፣ ቬንቸር ካፒታል፣ የመሳሪያ ሊዝ፣ ግምጃ ቤት ሰነድ፣ የፕሮጀክት የወጪ ፋይናንስን፣ የኮንትራት ማኑፋክቸሪንግ ጨምሮ ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት አሠራርና ሥርዓት ይዘረጋል፣

- ከጡረታ፣ ኢንሹራንስና ማህበራዊ ዋስትና የሚሰበሰቡ ገንዘቦች ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ስጋትን ባገናዘበ መልኩ ከባንኮች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራበት አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

## 4.5 የማክሮ ኢኮኖሚና ቢዝነስ ስነ-ምህዳር

የአምራች ኢንዱስትሪው ምርታማና ተወዳዳሪ እንዲሆን ተገማች የማክሮ ኢኮኖሚና አስቻይ የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር መፍጠር ዋና የፖሊሲ ጉዳይ ሲሆን የፖሊሲ ጉዳዩ አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.5.1 ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ

የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እጅግ ተፈላጊ ከሆኑ መሠረታዊ ሁኔታዎች አንዱ ነው:: መንግሥት የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የዋጋ ግሽበትን፣ የወለድ ምጣኔና የውጭ ምንዛሬ ተመንን በተመለከተ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን አውጥቶ ሲተገብር ቆይቷል:: ሆኖም የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂክ ትግበራዎች የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን በሚፈለገው መልኩ አልፈጠረም:: የዋጋ ግሽበት ከነጠላ አሀዝ በላይ መሆኑ፣ የውጪ ምንዛሪ ፖሊሲ ተገማች አለመሆንና የአቅርቦት እጥረት፣ የዕዳ ጫና እንዲሁም ለመንግስት ኢንቨስትመንትና ለአገልግሎት ዘርፍ ያደላ የፋይናንስ ሥርዓት መፈጠሩን ለአብነት መመልከት ይቻላል:: ይህም ባለሃብቱ በረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት ከመሳተፍ ይልቅ በአጭር ጊዜ ትርፍ በሚያስገኙ የኢኮኖሚ እንቅስቅሳሴዎች ላይ እንዲያተኩር አድርጎታል:: በሌላ መልኩ የውጪ ምንዛሬ ፖሊሲ ትግበራ የአምራች ኢንዱስትሪውን በሚያበረታታ መልኩ አልተመራም:: በሀገር ውስጥ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን የሚመልስ የማክሮ ኢኮኖሚ ስጋት ስራ አመራር ሰርዓት በተገቢው መልኩ አልተመራም:: እነዚህን የፖሊሲ ክፍተቶች እና በዘርፉ ላይ የተፈጠረውን ተግዳሮት ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

- መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪ በተለይም ከፍተኛ የመዋለንዋይ ፍሰት የሚያስፈልገው እንዲሁም ውጤቱንም ለማየት ረዥም ጊዜ መጠየቁን ባገናዘበ መልኩ የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፍ የተረጋጋና ተገማች የማክሮ ኢኮኖሚ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል::

- ዝቅተኛ የዋጋ ግሽበት፣ ተገማችና የተረጋጋ የውጪ ምንዛሪ ተመን፣ የወለድ ምጣኔ እና ሚዛናዊ የፋይናንስና የሀብት ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ ይደረጋል::

- በሀገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን መቋቋም የሚያስችል የማክሮ ኢኮኖሚ ስጋት የሥራ አመራር ተግባራዊ ይደረጋል::

- የማክሮ ኢኮኖሚ አስቻይ ሁኔታዎች ሀገሪቱ ያላትን ዕምቅ አቅምና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የምትሆንባቸውን ምርቶች በሚደግፍና በልዩ ሁኔታ ያለባቸውን መዋቅራዊና አቅም አጠቃቀም ክፍተት ለመፍታት በሚያስችል መልክ እንዲሆኑ ይደረጋል::

### 4.5.2 4.1.2 ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አስቻይ የንግድ ሥራና ኢንቨስትመንት ሥነ-ምህዳር

ምቹ የንግድ ሥራ ከባቢ መፍጠር በአምራች ኢንዱስትሪው ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት እንዲኖር እንዲሁም የምርት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሚያስችልና የሚያበረታታ ዝቅተኛው መስፈርት ነው:: መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በግል ዘርፉ የሚመራ በተለይም የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ ላይ ያተኮረ እና ከሀገር ውስጥ ባለሃብት ጋር መዋዕለ-ንዋይ ማፍሰስን የሚያበረታታ አሰራር ዘርግቷል:: የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር አዋጅ የፓርኮች ልማት በመንግስትና በግል ዘርፉ እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል:: በየጊዜው

የተሻሻሉት የኢንቨስትመት እና የንግድ ሕጎች ቀልጣፋ የንግድ ሥራ ስርዓት ደረጃን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች ለአምራች ኢንዱስትሪው ተጨማሪ አስቻይ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ባገናዘበ ሁኔታ የሀገር ውስጥ አምራች ድጋፍና ማበረታቻ፣ የክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የውጭ ኢንቨስተሮች ጥራት ክትትል እና የግብዓት ትስስር በተጠናከረ የአሰራር ስርዓት መምራት ያስፈልጋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ የንግድ ሥራና ኢንቨስትመንት ከባቢ (የፓርኮችና ሌሎች የኢኮኖሚ ዞን መዘርጋትን ጨምሮ) ቀልጣፋና ግልፅ እንዲሆን በማድረግ የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ያስፈልጋል። ይህም የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ የሀገር ውስጥ አምራች እና የውጪና የሀገር ውስጥ አምራች ሽርክናን ባገናዘበ ሁኔታ የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መሳብ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ የታክስ ምዝገባ እና የደረሰኝ ግብይት ቁጥጥር ስርዓት የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት ማጠናከር አስፈላጊ ነው። የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረቻ ቦታ አቅርቦት አሰራር በተለይም የመንግስት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለውጪ ንግድ ኢንቨስትመት ትኩረት ከማድረጉ በተጨማሪ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ላይ የተሳተፉ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በተጠናከረ መልኩ ማበረታታትና መደገፍ ያስፈልጋል። የመንግስት ኢንቨስትመንት በግሉ ዘርፍ ሊተገበሩ የማይችሉትን ስትራቴጂክ ምርቶች አዋጪነቱን ባገናዘበ መንገድ የገበያ ጉድለቱን መሙላት እንዲሁም የመንግስትና የግሉን ዘርፍ አጋርነት በሚያበረታታና በሚያሰፋ መልኩ መምራት አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ስርዓቱ የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ ይዘረጋል። ይህም የሀገር ውስጥ አምራች፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ የውጪና የሀገር ውስጥ አምራች ሽርክና እና የኮንትራት ማኑፋክቸሪንግ በሚያበረታታ መልኩ የአሰራር ሥርዓቶች ይዘረጋሉ፣ ይጠናከራሉ።

- የግል ዘርፉ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ከመንግስት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ግንኙነት ለማጠናከር የአምራች ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ከሁሉም የአምራች ዘርፉ ማህበራት በማውጣጣት ይቋቋማል።

- የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚያሳድግ አስራር ሥርዓት ይዘርጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የታክስ ምዝገባ እና የደረሰኝ ግብይት ቁጥጥር ሥርዓት የሚያስተሳስር የአሰራር ሥርዓት እና የንግድ ሥራ ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል።

- የኢንዱስትሪ ፓርክና የክላስተር ማዕከላት አሰራር በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በግሉና በመንግስት የጋራ ቅንጅት እንዲለማና እንዲመራ ይደረጋል፣ የቴክኖሎጂና ክህሎት ሽግግር እና የግብዓት ምርት ትስስር እንዲጠናከር ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

- የመንግስት ኢንቨስትመንት በግል ዘርፉ ሊሰሩ የማይችሉትን ዘርፎች እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ሊሳተፍባቸው የሚችሉ ሆኖም ግን የግሉ ዘርፍ ያልተሳተፈባቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች በቅድመ አዋጭነትና የውጤታማነት መከታተያ የተጠናከረ ሥርዓት በመዘርጋት መንግስት

ስትራቴጂክ በሆኑ ምርቶች ላይ ብቻውን ወይም ከግል ባለሃብቱ ጋር በቅንጅት የገበያ ጉድለቱን ይሞላል። የግሉ ዘርፍ እና የገበያ አቅም ሲዳብር በሂደት ይወጣል።

### 4.5.3 4.1.3 ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ማሳደግ

መሬት የአምራች ኢንዱስትሪውን ዕድገት ለማሳካት ስትራቴጂክ የመሠረተ ልማት ሲሆን በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ማቅረብ የተመቻቸ የቢዝነስ ምህዳር ለመፍጠር ወሳኝ ነው። ነገር ግን መሬት ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚከለልበትና በኢንቨስትመንት አይነቶች ተለይተው በምን ያህል ዋጋ እና መጠን መሬትን ማግኘት እንደሚቻል የሚያሳይ አሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም። ይህም የመሬት አቅርቦት የአካባቢውን ማህበረሰብ ለዘላቂ ልማትና ተጠቃሚነት አካታችነትን ያላገናዘበ እና የመሬት ማካካሻ ሥርዓት የግልፅነትና ወጥነት (በተለይም በፌደራል እና በክልልና በከተማ አስተዳደር ተዋረድ መዋቅር ጨምሮ) ክፍተት ፈጥሯል። በመሆኑም መሬት ለአምራች ኢንዱስትሪው የማቅረብ ሂደት ረዥም፣ ግልፅነት የጎደለው እና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ እንዲሆን አድርጎታል። የማምረቻ ቦታ አቅርቦት አሠራር በተለይም የመንግሥት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለውጪ ንግድ ላይ ብቻ በማተኮሩ በተኪ ምርት ላይ የተሳተፉ የሀገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታታና የሚያሳትፍ አልነበረም። በሌላ መልኩ ለጥቃቅንና አነስተኛ አምራቾች የማምረቻ ቦታ አቅርቦት የአሠራር ሥርዓት የግልፅነትና ተጠያቂነት ማዕቀፍ በተሟላ መልኩ አልተቀመጠም። ስለሆነም በዚህ ፓሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን፤

- የአምራች አንዱስትሪዎች የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት የኢንዱስትሪ ማፐን የተመርኮዘ ሆኖ የኢንዱስትሪ ክላስተሮችንና የአካባቢዎችን ዕምቅ ኢንዱስትሪ አቅም ያላቸውን አካባቢዎች ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ይደረጋል።

- የኢንዱስትሪ ክላስተሮች የአካባቢ ልማት ዕቅድ ጋር እንዲጣጣም እና ከመሬት/የማምረቻ ቦታ፣ የውሃ፣ የኤሌክቲሪክ ሃይል አቅርቦት፣ የመኖሪያ ቤት ልማት እና ማህበራዊ አገለግሎት አቅርቦት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

- ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን መሬት ከይገባኛል ነፃ ተደርጎ፣ ሁሉም መሰረተ ልማቶች ተሟልተውለት በዝቅተኛ ዋጋ በዘርፉ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች ይቀርባል።

- በየደረጃው የሚገኙ የክልልና የከተማ አስተዳድሮች ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን መሬት ለኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ለልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እና ለኢንዱስትሪ ከተከለሉ ቦታዎች ውጭ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እንዲያቀርቡ ድጋፍ ይደረጋል።

- ለአነስተኛና ጥቃቅን የአምራች ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚሆን የመስሪያና የመሸጫ ቦታ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላት አንዲቀርብ ይደረጋል።

- ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ ፓርክ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሁም ከዚህ ውጭ በግል ባላሀብቱ የሚለሙ መሬቶች የአካባቢውን የመልማት ፀጋ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ይደረጋል።

- የአምራች አንዱስትሪዎች የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት በፌደራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ተዋረድ መዋቅር ተጠያቂነት ያለበት፣ ባለሃብቱ የተሰጠውን የመሥሪያ ቦታ ለታለመለት ዓላማ ማዋሉን የሚያረጋግጥ፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለዘላቂ ልማትና ተጠቃሚነት አካታችነትን ያገናዘበ እና አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥና ግልጽ አሠራር እንዲዘረጋ ይደረጋል።

### 4.5.4 4.1.4 ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት ማሳደግ

ለአምራች ኢንዱስትሪ አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት ማረጋገጥ ለኢንዱስትሪው ዕድገት የማይተካ ሚና አለው። መንግሥት የኤሌክትሪክ ሃይል ለአምራች ኢንዱስትሪ ለማቅረብ የተለያዩ የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በመጠቀም ኃይል ማመንጨትና ማሰራጨት በስፋት ቢያከናውንም የአምራች ኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ (በቂና ያልተቆራረጠ) የኃይል አቅርቦትን የሚመራበት በአምራቹና በኃይል አቅራቢው መካከል የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪው ለአዳዲስና ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ኃይል ለመዘርጋት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች ለመገንባት የሚያስችል የማበረታቻና የማስፈፀሚያ አሠራር ሥርዓት አልዳበረም።

በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪውን አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዳይኖረው እና ለተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ ዳርጎታል፤ ይህም ዝቅተኛ የአቅም አጠቃቀም እና ከፍተኛ የማሽን ብልሽት በማስከተል ኢንዱስትሪው ዝቅተኛ ምርታማነት እንዲኖረው ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ ሆኗል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

- የአምራች አንዱስትሪዎችን የኃይል ፍላጎት መሰረት ያደረገ፣ በቂና ያልተቆራረጠ እና የኢንዱስትሪ ክላስተርን የተከተለ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል።

- የአምራች አንዱስትሪዎች የኃይል አቅርቦት በፌደራልና በክልል ተዋረድ መዋቅር ተጠያቂነት ያለበት፣ አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥና ግልጽ አሠራር የሚከተል እንዲሆን ይደረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ ኃይል የሚያመነጭበትና የሚጠቀምበት ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል፣ እንዲሁም የፋይናንስ አቅርቦት ይመቻቻል።

- በአምራች ኢንዱስትሪውና በኃይል አቅራቢው መካከል የኃይል ግዥና ሽያጭ የውል ስምምነት (በኃይል መቆራረጥ ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን ተጠያቂ የሚያደርግ እና ምላሽ የሚሰጥበት አሰራርን ጨምሮ) ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.5.5 ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አቅርቦት ማሻሻል

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ስኬታማነት ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉ አስቻይ ሥነ ምህዳር አንዱ አስተማማኝ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋና ቅልጥፍና ከዘርፉ ልዩ ባህሪያት ጋር በተስማማ ሁኔታ ማቅረብ ሲቻል ነው። ለዚህም መንግሥት የመንገድ መረብ ማስፋት በተለይም ደረጃውን የጠበቀ የመንገድ ዝርጋታና ጥገና አካሂዷል። ይሁን እንጂ የሀገራችን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ዝርጋታ የኢንዱስትሪ ልማቱን የተከተለ

አለመሆን እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ብቃት ዝቅተኛ መሆን፣ ከሌሎች ተወዳዳሪ ሀገራት ጋር ሲታይ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ እንዲሁም የተሟላ የኃላፊነትና ተጠያቂነት የአሠራር ሥርዓት አልተዘረጋም። በተጨማሪም የሎጀስቲክስ አገልግሎት አቅርቦት ውስን በሆኑ አገልግሎቶች ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ዘመናዊ የምርት ማጓጓዥያ፣ ፓኬጂንግ፣ የመጋዘን አስተዳደር አገልግሎት፣ የትራንስፖርት አስተዳደር አገልግሎት እና የኢንቬንቶሪ አስተዳደርን ማቅረብ የሚያስችሉ አሠራሮች በበቂ ሁኔታ አላደጉም። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ ትልቅ የዘርፉ ተግዳሮት ሆኗል። እነዚህን ዋና ዋና የፖሊሲ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

- የአምራች አንዱስትሪዎች የትራንስፖርት ዝርጋታና አገልግሎት አቅርቦት የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ የሚያግዝ ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፋ ይደረጋል።

- የአምራች አንዱስትሪዎች ሎጂስቲክስ ዝርጋታ እና አገልግሎት አቅርቦት የኢንዱስትሪ ልማት የተከተለ እና የሚደግፍ እንዲሆን ይደረጋል።

- በየደረጃው የኢንዱስትሪ ግብዓቶች የሚገኙባቸውን አካባቢዎችና አግሮ ኢንዱስትሪዎችን የሚያስተሳስሩ መጋቢ መንገዶች እና የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መሰረተ ልማቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲለሙ ይደረጋል።

- የአምራች አንዱስትሪዎች የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ የሚያግዝ ዘመናዊና ተጨማሪ ሎጂስቲክስ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ይደረጋል፣ ይህም በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥት ጠንካራ አጋርነት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

### 4.5.6 ለአምራች ኢንዱስትሪ የጉምሩክ አገልግሎት አቅርቦት ማሻሻል

የአምራች ኢንዱስትሪ የገቢና ወጪ ንግድ ለማሳለጥ የጉምሩክ አገልግሎት አንዱ አስቻይ ሁኔታ ነው። መንግስት አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለማቅረብ እና አለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም የተለያዩ ማሻሻያዎች ተተግብረዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበና ቀልጣፋ የጉምሩክ አሰራር በተለይም የማምረቻ ግብዓት ትመና ፣ የግብዓት ምርት ጥምርታ፤ የግዢ ደረሰኝ ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የአሰራርና ቁጥጥር ሥርዓት እና የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ስርዓት ማዘመን ያስፈልጋል። በተጨማሪም የማምረቻ ግብዓት ትመና ክህሎት፣ ግልፅና ወቅታዊ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ፣ የጉምሩክ ባለሙያ እና የጉምሩክ አስተላላፊ ተጠያቂነት፣ የቀረጥና ታክስ ድህረ ክፍያ፣ የተገልጋዮች የአገለግሎት መስጫ ጊዜ ስታንዳርድ፣ የተመረጡ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች አገልግሎት፣ የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር እና ኮንትሮባንድ ቁጥጥር ማሻሻል አስፈላጊ ናቸው። በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የጉሙሩክ አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለማቅረብ እና ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የተሟላ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የማምረቻ ግብዓት ትመና፣ የጉሙሩክ አሠራር

ሥርዓት (ድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት እና የግዢ ደረሰኝ ትክክለኛነት ማረጋገጫ) እና የሥራ ሂደት ቀልጣፋ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

### 4.5.7 የአምራች ኢንዱስትሪ የማበረታቻ ስርዓት ውጤት ተኮር ማድረግ

መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን እና ለባለሃብቱ የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር የተለያዩ የማበረታቻ ሥርዓቶችን ዘርግቷል፡፡ የማበረታቻ ሥርዓቶቹ የአምራች ኢንዱስትሪውን ልዩ ባህሪያት ያገናዘቡ እና የማበረታቻው ውጤታማነት የሚለካበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ የሚዘረጋው ውጤት ተኮር የማበረታቻ ስርዓት የሀገር ውስጥ ባለሃብትን በሰፊው በሚስብና በሚያበረታታ መልኩ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የመንግስትን ውስን ሃብት በአግባቡ ለማስተዳደር ብሎም የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለይቶ በማበረታታት ለዘርፉ ዕድገት ቀጥተኛ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ያስችለዋል፡፡

- የአምራች ኢንዱስትሪ የማበረታቻ ሥርዓት የሀገር ሀብትን በሚቆጥብና ለዘርፉ ዕድገትና ውጤታማነት የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ሆኖ በውጤት ላይ የተመረኮዘ የማበረታቻ ሥርዓት ይተገበራል፤ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

- ሀገሪቱ ያላትን ዕምቅ አቅምና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በምትሆንባቸው ምርቶች ላይ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች በተለየ ሁኔታ የማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.5.8 ለአምራች ኢንዱስትሪ የተመቸ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግስት አገልግሎት ማቅረብ

የመንግስት አገልግሎት በተዋረድ መዋቅሮች ግልጽ፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና፣ በሕግና በአስተዳደራዊ ሂደት ተጠያቂነት ያለበት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋት አንዱና ዋነኛው መደላድል ነው፡፡ መንግስት ጠንካራ የአመራር ሚና የሚጫወትበት አቅጣጫ እና ግልፅ፣ ተጠያቂና ቀልጣፋ አገልግሎት ማቅረብ፣ ልማትን የሚደግፍ የግብር እና መረጃ ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም ቀልጣፋ የፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መፍጠር ለኢንዱስትሪ ቀጣይነት ያለው ሚና ወሳኝ በመሆኑ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጨምሮ የተለያዩ ሥርዓቶች ተተግብረዋል፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የመንግስት አገልግሎት ሊያቀርብ የሚችል የመንግስት ሠራተኛ ተጨማሪ የማትጊያና ተጠያቂነት (ውጤታማነት መከታተያ) ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ የመንግስት ተቋማት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው የሚሰሩበት የቅንጅትና ተጠያቂነት አሰራር መዘርጋትና የተልዕኮ ግጭት ማስቀረት ቀልጣፋና ተጠያቂ የሆነ የመንግስት አገልግሎት እና ለባለሀብቱ በቂ ድጋፍና ክትትል ለማካሄድ ወሳኝ ነው፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን የሚመራ የመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል መምራትና የአምራች ኢንዱስትሪ ንቅናቄ መፍጠር ይጠይቃል፡፡

- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ የመንግሥት አገልግሎቶች አቅርቦት አሠራር ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፣ የአምራች ኢንዱስትሪው በጠንካራ ቁጥጥር ሥርዓት እና በተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት እና በመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ የመንግስት ተቋማት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው የሚሰሩበት የቅንጅትና ተጠያቂነት አሰራር ይዘረጋል።

- የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት የተሳለጠና የተሰናሰለ የአንድ መስኮት አገልግሎትን ማጠናከር፣ የመንግስት አገልግሎት ጥራት ስራ አመራር፣ የዲጂታል አገልግሎት፣ የተገልጋዮች የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ስታንዳርድ፣ የተመረጡ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ጨምሮ ይሻሻላል፣

## 4.6 የአካባቢ እና ማህበራዊ አካታችነትና ዘላቂነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን አካታችነትና ዘላቂነት ማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በመሆኑ ከላይ በቀረቡት ዋና ዋና ፖሊሲ ጉዳዮች ውስጥ ተካተው የሚተገበሩ ይሆናሉ። በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪ የአካባቢ ዘላቂነት ለማሳደግ እና የሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኛ ተሳትፎ፣ አበርክቶና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የፖሊስው ጉዳዮችና አቅጣጫ ተለይተዋል።

### 4.6.1 የአምራች ኢንዱስትሪ የአካባቢ ዘላቂነት ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪዎች የአመራረት ስልት ከአካባቢ ጋር የተዛመደ፣ የማኅበረሰቡን ደኅንነት የሚጠብቅ ማድረግ እንዲሁም ዓለም ዓቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶች ያገናዘበ እና ሀገራዊ የአካባቢ ሕጎችና መመዘኛ መስፈርቶችን ማሟላት ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ ሚና አለው። የአምራች ኢንዱስትሪ ዘላቂ የማምረት ሂደት እንዲከተል እና ግብዓት ወይም ምርት ደጋግሞ ጥቅም ላይ የሚያውል፣ ግብዓት መጠን የሚቀንስና በተገቢው መንገድ የሚያስወግድ (በተለይም ኬሚካል) እና ዝቅተኛ ተረፈ ምርት ያለው ሆኖ ምርታማነትን የሚያሳድግ እና የአካባቢ ብክለት የሚቀንስ ይሆናል። መንግስት የአካባቢ ፖሊሲ ማዕቀፍ እና ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ተተግብሮ ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍና የሚያበረታታ ሥርዓት ተዘርግቷል።

ይሁን እንጂ የአምራች አንዱስትሪ ሰርኩላር ምርት ሥርዓትን፣ ዘላቂና አረንጓዴ ማምረት ሂደትን ጨምሮ ለማሳደግ የተሟላ ድጋፍና ማበረታቻ እና የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲሁም የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት አልተዘረጋም። በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪው የአካባቢ ብክለት እያስከተለ ይገኛል፤ የዘርፉ ምርት ተወዳዳሪነት ላይ፣ በተለይም ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር የሚፈለጉ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን አሟልቶ ወደ ውጪ መላክ ጨምሮ ክፍተት ፈጥሯል። እንዲሁም የኢንዱስትሪው የአካባቢ ህብረተሰብ ጤና መታወክ አስከትሏል። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የአምራች አንዱስትሪ የሰርኩላር ምርት ሥርዓትን የሚደግፍና የሚያበረታት እንዲሆን ይደረጋል።

- የሰርኩላር ምርት አመራረት ስርዓትን እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሠራር እንዲኖረው ይደረጋል።

### 4.6.2 በአምራች ኢንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 35 ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካው ዘርፍ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ከወንድ እኩል መብት እንዳላቸው በግልፅ ያስቀምጣል። እነዚህን የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መንግስት ሁለንተናዊ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሴቶች ፖሊሲ እና የሴቶች የልማትና የለውጥ ስትራቴጂ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል፣ ማሻሻያዎችም ተደርገባቸዋል። በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሴቶች ከኢንዱስትሪ ባለቤትነት እስከ ቋሚ የሥራ ተቀጣሪነት ድረስ ያላቸዉ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። በተጨማሪም የሴቶች ጉዳይ በልማት ዕቅዶች ውስጥ በባለ ብዙ ዘርፍ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል።

ሆኖም ግን የአምራች አንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የፋይናንስ፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የመሬት፣ የኃይል እና የቴክኖሎጂ አቅርቦት በተለየ የሚደግፍና የሚያበረታታ የማስፈፀሚያ አሠራር አልተዘረጋም። እንዲሁም ሴቶችን በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሳብና ለመደገፍ አስቻይ ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ አልተመቻቹም። በዚህም የሚጠበቀውን የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አልተቻለም፤ የባለቤትነትና አመራር ሰጪነት ድርሻም አነስተኛ ሆኗል። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚከሉት የፖሊሰ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የአምራች አንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የሚደግፍና የሚያበረታት እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሠራር እንዲኖረው ይደረጋል።
- የሴት አምራቾች የመሬት አቅርቦት፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አጠቃቀም፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲሁም ገበያ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።

### 4.6.3 በአምራች ኢንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

መንግስት ሁለንተናዊ የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ዘርግቷል፣ ማሻሻያዎችን አድርጓል። በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወጣቶች በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤትነት እንዲሁም በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ውስጥ ቋሚ የሥራ ተቀጣሪነት ያላቸዉ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

ሆኖም ግን የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች አዲስ ፈጠራ የሚደግፍና የሚያበረታታ አሰራር በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም፣ በተለይም አዲስ የፈጠራ ሃሳብ የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ፍጥሯል። በተጨማሪም የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ የክትትልና ማስፈፀሚያ አሰራር አልተዘረጋም። ይህም ወጣቶች በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሳብና ለመደገፍ አስቻይ ሁኔታዎች ባለመመቻቸቱ የሚጠበቅን ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አልተቻለም፣ ከፍተኛ የተማረ እንዲሁም ያልተማረ የወጣት ስራ አጥነት ተንሰራፍቷል። እነዚህን ክፍተቶች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሰ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የሚደግፍና የሚያበረታት እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል።

- ወጣት አምራቾች የመሬት አቅርቦት፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፈጠራና አጠቃቀም፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲሁም ገበያ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።

## 5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች

***ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፦*** *የአምራች ኢንዱስትሪው በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን የማምረት አቅምን፣ ቅልጥፍናንና ምርታማነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው። የማምረት አቅምን ለማሳደግ የግብዓት አቅርቦትን ከመጀመሪያ የግብዓት አቅራቢ ዘርፎች ማለትም ከግብር እና ከማዕድን ጋር በመቀናጀት የመለየት እንዲሁም የማልማት ስራን ይጠይቃል። በሌላ በኩል በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን የግብዓት ትስስር ለማሳደግ በዘርፉ የሚገኙ ላዕላይ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የግብዓት ተመጋጋቢነትን የሚያበረታቱ ኢንቨስትመንቶችን በመለየትና በመሳብ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ይሰራል። በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ማፐን እና የአካባቢያዊ አቅምን መሰረት ባደረገ መልኩ የኢንዱስትሪ ክላስተሮችን የመሰረተ ልማት፤ የሰውና የካፒታል ሃብት አቅርቦትን እንዲሁም አጠቃቀምን ምርታማነት ሊያሳድግ በሚችል መልኩ በማደራጀትና በማዋቀር የምርትና ምርታማነት የውጤት መስክ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።*

***የአምራች ዘርፍ አቅም ማሳደግ፦*** *የአምራች ኢንዱስትሪውን አንጻራዊ የምርት ብልጫ በተለይም የተወዳዳሪነት ብልጫን ለማምጣት የዘርፉን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ፈጠራን በምርምርና ስርጸት በማሳደግ ዘርፉን በአለም አቀፍ ደረጃ በምርት ስብጥር፣ ጥራት፣ እንዲሁም በምርታማነት ተወዳዳሪ ለማድረግ ይሰራል። ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚመጥን እውቀት እና ክህሎት ያለው የሰው ሀይል በብዛትና በጥራት ለማቅረብ የኢንዱስትሪ ባህልን የሚያዳብሩ የካሪኩለም እና የትስስር ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን የኢንዱስትሪ ክህሎት እና ባህልን የሚያዳብሩ አጫጭር መካከለኛ እና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በመቅረፅ የሚተገበሩ ይሆናል። ይህም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ልማት አገልግሎቶችን (BDS) ድጋፍ ማዕቀፍችን በማዘጋጀት ተግባራዊ የሚደረግ ነው።ለዚህም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ፈጠራን የሚያሳድግ፣ የጥናትና ምርምር ማዕከላትን አቅም የሚያጎለብት፤ አምራች ኢንዱስትሪውን ያማከለ የቴክኖሎጂ መፈልፈያ እና ማበልፀጊያ ማዕከላትን መፍጠር እና ማስፋፋት የዚህ የትኩረት አቅጣጫ ግብ ነው። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ኮሜርሻላይዜሽን ስርዓት መዘርጋት እና ማጠናከር ሌላው የዚህ የውጤት መስክ ማሳያ ነው።*

***የአምራች ኢንዱስትሪ የኤክስፖርት ምርት ስብጥር እና የስትራቴጂክ ተኪ ምርቶች ያላቸውን ድርሻ ማሳደግ፦*** *የኤክስፖርት ምርት ስብጥርን በጥራትና በብዛት በማስፋትና በማጠናከር፣ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ፣ እንዲሁም ዘላቂ ውጤት ተኮር የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት የዘርፉን የኤክስፖርት ድርሻ በማሳደግ የሀገሪቱን የንግድ ሚዛን የሚያሻሽሉ ስትራቴጂክ ምርቶችን በጥናት በመለየት በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በሽርክና የኤክስፖርት እና ተኪ ምርቶችን በማልማት ለውጪ እና ለሃገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ሌላው የዚህ ፖሊሲ የውጤት መስክ ተደርጎ ተለይቷል።*

***ዘላቂ የማኑፋክቸሪንግ ስርዓት መዘርጋት፦*** *የአምራች ኢንዱስትሪ ዘላቂ የማምረት ሂደት ሊከተል የሚያስችል (ግብዓት ወይም ምርት ደጋግሞ ጥቅም ላይ የሚያውል፣ ግብዓት መጠን*

የሚቀንስና በተገቢው መንገድ የሚያስወግድ እና ዝቅተኛ ተረፈ ምርት ያለው እና የአካባቢ ብክለት የሚቀንስ (Circular Economy) ስርዓት በመዘርጋት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አመራረት ስልት የማኅበረሰቡን ደኅንነት የሚጠብቅ በማድረግ ፣ዓለም ዓቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶች ያገናዘበ እና ሀገራዊ የአካባቢ ሕጎችና መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟላ በማድረግ እንዲሁም የሴቶችና ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞችን ያማከለ በማድርግ ዘርፉን ዘላቂ እና ተወዳዳሪ ማድረግ አንዱ የትኩረት መስክ ነው፡፡

## 6. የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን

ይህን የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሀሳብ አመንጭነት ተዘጋጅቶና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይህ ፖሊሲ የጥቃቅን፣ የአነስተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችንና ኢንዱስትሪዎችን ይመለከታል፡፡

## 7. የፖሊሲው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

### 7.1 ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት ዋና ዋና አስፈፃሚ አካላት ይኖሩታል፡፡

- በየደረጃው የሚገኙ የክልልና የከተማ አስተዳድሮች ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን መሬት ለኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ለልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እና ለኢንዱስትሪ ከተከለሉ ቦታዎች ውጭ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት ከይገባኛል ነፃ አድርገው የማቅረብ ሀላፊነት ሲሆን በተጨማሪም ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የሰው ሀይል በጥራትና በስፋት ማቅረብ ናቸው፡፡

- የግብርና ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር ፦ ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ የግብርና እና የማዕድን ምርቶችን በመለየት በጥራትና በብዛት በማምረት ያቀርባል፤ በአምራች ዘርፉ የሚመረቱ ምርቶችን ለግብርናው እና ለማዕድን ዘርፎች በግብዓትነት በመጠቀም የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪው እንዲነቃቃ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም አምራች ኢንዱስትሪው በጠንካራ መሰረት ላይ እስከሚቆም በቅድሚያ የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጎት በማሟላት ቀሪውን የግብርና እና የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ለአምራች ኢንዱስትሪው የውጭ ምንዛሬ ያቀርባሉ፡፡

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፦ ለአምራች ኢንዳስትሪዎች በቂ፣ አስተማማኝ እና ጥራት ያለው የሀይል አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፤ ከመንግስት ከሚቀርበው ሀይል ባሻገር ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን የሀይል አማራጮች የሚያገኙበትን አግባብ ይቀይሳል፣ ለዚህም የሚሆኑ የማበረታቻ ማእቀፎችን ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ በመሆን ለአምራች ኢንዱስትሪው ይሰራል፡፡

- የትምህርት ሚኒስቴር፣ ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፦ ለአምራች ኢንዱስትሪው ብቁና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል ያቀርባል፤ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ ያገኙትን እውቀት በተግባር እንዲተገበሩ የኢንዲስትሪ ዩኒቨርሲቲ ትስስር መርሀ ግብሮችን በመቅረፅ በተግባር በማዋል

የሰለጠነ የሰው ሀይል ያቀርባሉ። ከዚህም በተጨማሪ የአምራቹን ማህበረሰብ ማነቆ የሚፈታ እና ገበያውን ማእከል ያደረገ የምርምር እና ስርጸት ፕሮግራሞችን የመምራት፣ የመስራት እና የማስተባበር ኃላፊነቶች ይኖርባቸዋል።

- የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር፦ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ለማጓጓዝ የሎጂስቲክስ እና ትራንስፖርት አሰራሮችን ማቀላጠፍ እና ማዘመን፣ ወደ ውጭ የሚወጡ እና የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን እና ግብአቶች የወደብ ቆይታን በማሳጠር ወጪን በመቀነስ የአምራች ኢንዱስትሪው ትርፋማ እንዲሆን ማገዝ ዋና ዋና ተግባራቶቹ ይሆናል።

- የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የከተማ መስተዳድሮች፦ የመሬት አቅርቦት ለአምራች ኢንዱስትሪው ፍትሀዊ በሆነ ዋጋ በማቅረብ ምርት ትኮር የኢንዱስትሪ ክላስተር የኢንዱስትሪ ማፑን እና የአካባቢ እምቅ አቅም ባማከለ መልኩ መዘርጋት እና ማስተባበር፣ እንዲሁም ለኢንዱስትሪዎች የሚያገለግሉ የመሰረተ ልማቶች የሚመለከታቸውን በማስተባበር ለአምራቾች እንዲሟሉ ማድረግ። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የሰው ሀይል በጥራትና በስፋት ማቅረብ ናቸው።

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የአምራች ኢንዱስትሪውን ውጤታማ ሊያሰደረጉ የሚችሉ ብቃትና ጥራት ያላቸውን ኢንቨስትመመንቶች ለመሳብ የሚያስችል የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራ ማስተግበርና መስራት፣ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የማበረታች ስርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ ማስተባበር፤ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና በስራ ላይ ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች በትክክል ስለመስራታቸው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እና ተገቢነት በሌላቸው ኢንዱስትሪዎች እና አምራቾች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይወስዳል።

- ብሄራዊ ባንክ፦ የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማበረታታት የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ ምደባ ቅድሚያ ይሰጣል፤አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሬ ሙሉ ለሙሉ ተጠቅመው ስራቸውን ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤የግል ባንኮችም ከሚያበድሩት ብድር ቅድሚያ ለአምራች ኢንዱስትሪው ለመስጠት አስገዳጅ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።

- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፦ የአምራች ኢንዱስትሪዎች በሀገር ላይ የሚያሳድሩትን የአካባቢ ብክለት ሊቀንሱ የሚችልበትን አሰራር ይዘረጋል፤ተግባራዊም ያደርጋል። እንዲሁም የበካይ ተረፈ ምርቶችን የሚያስተናግዱበትን አሰራር ይከታተላል፤ በማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው ብሎ ሲያምን በህግ አግባብ የሚዳኙበትን አሰራር ይዘረጋል።

- የገቢዎች እና የገንዘብ ሚኒስቴር፦ አምራች ኢንዱስትሪውን ለማበረታታት የተፈቀዱ እና የሚፈቀዱ ከቀረጥ ነፃ አገልግሎቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ ውጤት ተኮር የማበረታች አሰራሮችን ከሌሎች ባላድራሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ይዘረጋሉ። በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን በአገር ውስጥ መጠቀም ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚያበረታቱ ስርዓቶችን

ይዘረጋሉ። የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት የሚያስችሉ የሀብት ምደባ ቅድሚያ እንዲሰጠው ያደርጋሉ።

- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፦ በሀገር ደረጃ የአምራች ዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከዘርፉ ተዋንያን ጋር በመሆን የመምረጥ፣ ማላመድ፣ የተላመዱትን ወደ ምርት እንዲገቡ እና በሰፊው እንዲመረቱ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ልማት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያከናውናሉ፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን የብልጫ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በጥናትና ምርምር ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፣

## 7.2 ፖሊሲውን ለማስፈፀም የተለዩ የህግ ማዕቀፎች

ይህንን ፖሊሲ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ አምስት አዋጆች፣ዘጠኝ ደንቦች እና ስምንት በተለያዩ ተቋማት የሚዘጋጁ መመሪያዎች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል።

**በአዲስ መልክ የሚወጡ አዋጆች፦** የፖሊሲ ተግባርን የሚወጣ የአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ በጠንካራ ቁጥጥር ሥርዓት እና የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት የሚመራበት አዋጅ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት፣ አሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት አዋጅ ናቸው።

የሚሻሻሉ አዋጆች፦ የአምራች ኢንዱስትሪ በአፈፃፀም ላይ የተመሠረተ የውጤት ተኮር የማበረታቻ ማዕቀፍ ሥርዓት አዋጅ ማሻሻያ ይደረግበታል።

በአዲስ መልክ የሚወጡ ደንቦች፦ መንግስት በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚያደርገውን የኢንቨስትመንት ደንብ፣የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ የመንግስት ተቋማት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው የሚሰሩበት የቅንጅት እና ተጠያቂነት ደንብ ፣የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ ደንብ፣የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና እና የምርምር ተቋማት ትስስር የሀገራዊ የተቋማት ትስስር የሕግ ማዕቀፍን በመመርኮዝ የማስፈፀሚያ ደንብ ፣የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ማቋቋሚያ ደንብ ፣የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ (local content) የተዘዋዋሪ የወጪ ንግድን በሚያበረታታ መልኩ የአምራች አንዱስትሪ ምርት ግብዓት አጠቃቀም ደንብ እና ሰርኩላር ኢኮኖሚ ደንብ ናቸው።

የሚሻሻሉ ደንቦች፦ የአምራች ኢንዱስትሪ የመሥሪያ ቦታ አቅርቦት ደንብ፣ የኢንዱስትሪ የፓርኮችና ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ደንብ የሚሻሻሉ ደንቦች ናቸው።

በአዲስ መልክ የሚወጡ መመሪያዎች፦ በአምራች ኢንዱስትሪውና በኃይል አቅራቢው መካከል የኃይል ግዥና ሽያጭ የውል ስምምነት (በኃይል መቆራረጥ ምንክያት የሚመጡ ጉዳቶችን ተጠያቂ የሚያደርግ. እና ምላሽ የሚሰጥበት አሰራርን ጨምሮ) ስርአ ይዘረጋልት ፣ባንኮች (ወለደ አልባ ባንኮች ጨምሮ) ለዘርፉ የሚያቀርቡት የብድር ድርሻ ከፍ እንዲያደርጉ እና ድልድሉም ተጠያቂነት እንዲኖረው የሚያበረታታ መመሪያ፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን

የብድር ዋስትና አይነቶች የሚያሰፋ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚቀርበው የውጪ ምንዛሬ ኢንዱስትሪው ከሚያስገኘው ወይም ከሚያድነው የውጪ ምንዛሪ መጠን መከታተያ ሥርዓት መመሪያ ሲሆን ይህም ከውጤት ተኮር ማበረታቻ ሥርዓት ጋር የተናበበ ይሆናል። በመጨረሻም ለአምራች ኢንዱስትሪው የኢንሹራንስ ሽፋን ማስፋት የሚያስችል መመሪያ በአዲስ መልክ መዘጋጀት የሚገባቸው መመሪያዎች ናቸው።

የሚሻሻሉ መመሪያዎች፦ የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ (የፖሊሲ ባንክ የውጪ ምንዛሪ የሚያገኝበትና የሚያስተዳድርበት አሰራርን ጨምሮ) የባንኮች የውጪ ምንዛሬ ድልድል፤አቅርቦት እና አጠቃቀም መከታተያ እና መቆጣጠሪያ መመሪያ እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ባገናዘበ መልኩ የመንግስት አገልግሎት ሊያቀርብ የሚችል የሲቪል ሰርቪስ የማትጊያና የተጠያቂነት ሥርዓት ማሻሻያ መመሪያ ናቸው።

### 7.3 ፖሊሲውን ለማስፈፀም የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች

**ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፦** የግብዓት ልማት ማሳደግ ፕሮግራም፣ ተደራሽ የመሰረተ ልማት እና የመንግስት አገልግሎት ፕሮግራም፤የአምራች ኢንዱስትሪውን ፋይናንስ አቅርቦት ማሳደጊያ ፕሮግራም ፣ የአምራች ዘርፍ የሰው ሃይል ልማት ማሳደግ ፕሮግራም፣ምርት ተኮር የኢንዱስትሪ ክላስተር እና የሃገር ውስጥ አምራቾች ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮግራሞች ተግራዊ ይደረጋሉ። የግብዓት ልማት ማሳደግ ፕሮግራም የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚከናወኑ ስራዎችን ለመደገፍ ተግባራዊ የሚደረግ ፕሮግራም ይሆናል። ይህ ፕሮግራም በዋናነት ለአምራች ዘርፍ ከግብርና እና ከማዕድን ዘርፍ የመጀመሪያ ደረጃ ግብአት አቅርቦት ልማትለማሳደግ፤ የኢንዱስትሪ ዘርፉ እሴት ሰንሰለት ግብአት ልማት በማዳበር እና የግብዓት ግብይት ስርዓት በመዘርጋት የአምራች ኢንዱስትሪ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ተግባራዊ ይደረጋል። ተደራሽ የመሰረተ ልማት እና የመንግስት አገልግሎት ፕሮግራም የአምራች ዘርፍ ዋና ማነቆ የሆኑ የመሰረተ ልማት እና የመንግስት አገልግሎቶችን በማዘመን በጥራት እና በቅልጥፍና የኢንደስትሪ ክላስተሮችን ማዕከል ባደረገ መልክ በልዩ ሁኔታ የልማት ስራዎችን ለመደገፍ የሚተገበሩ ናቸው የአምራች ኢንደስትሪው ዘላቂ የሆነ ፋይናንስ እንዲኖረው ለማድረግ በመደበኛ የፋይናንስ ስርዓት ውስጥ ለአምራች ኢንደስትሪ ከሚቀርበው ፋይናንስ በተጨማሪ ለዘርፉ በልዩ ሁኔታ ግብዓት እና የካፒታል እቃዎችን የአቅርቦት ማነቆዎችን ለመፍታት የሚከናወኑ ደጋፊ የአምራች ኢንዱስትሪ ፋይናንስ ፕሮግራም ተግራዊ ይደረጋል። ምርት ተኮር የኢንዱስትሪ ክላስተር ፕሮግራም የመልማት ጸጋን ባማከለ መልኩ ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚሆን የማምረቻ መሬት የመለየት፤ የማዘጋጀት፤ እና የማቅረብ ስራዎችን ለመደገፍ የሚተገበር ፕሮግራም ይሆናል። የሃገር ውስጥ አምራቾች ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮግራም ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት እና ማሳደግ ሲሆን በዋናነት በመሰረተ ልማት አቅርቦት፤ በስልጠና፤ እና በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በማቅረብ እና በማመቻቸት የሚከውን ይሆናል።

**የአምራች ዘርፍ አቅም ለማሳደግ፦** የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ፈጠራን ለማሳደግ የአምራች ዘርፍ የምርምርና ስርጸት ፕሮግራም የጥናትና ምርምር ማዕከላትን አቅምን ማጎልበት፤

አምራች ኢንዱስትሪውን ያማከለ የቴክኖሎጂ መፈልፈያ እና ማበልፀጊያ ማእከላትን መፍጠር እና ማስፋፋት እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ኮሜርሻላይዜሽን ስርዓቶች ማጠናከር በዚህ ፕሮግራም ስር የሚከናወኑ ንኡስ ፕሮግራሞች ይሆናሉ።የአምራች ዘርፍ በሰው ሀይል ልማት እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንዲሁም ፈጠራን ማሳደግ በዚህ ፓሊስ ተግባራዊ የሚደረግ ፕሮግራም ይሆናል። የሰው ሃይል ልማት ፕሮግራም ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚመጥን የክህሎት፣ የኢንዱስትሪ ባህልን የሚያዳብሩ የካሪኩለም እና የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ተግባሮችን እንዲሁም የየኢንዱስትሪ ክህሎት፤ ባህል፤ እና የማስፈፀም አቅምን የሚያዳብሩ የአጫጭር፤ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በዚህ ፕሮግራም የሚፈጸሙ ንኡስ ፕሮግራሞች ይሆናል። በተጨማሪም በዚህ ፕሮግራም ስር ለአምራች ዘርፍ በተለይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ልማት አገልግሎቶች (BDS) የድጋፍ ማእቀፍ ማዘጋጀት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ግኝትን/ፈጠራን እንዲያስፋፋና እንዲያስተዋውቅ የቴክኖ ፓርኮችን ማሳደግ እንዲሁም የሚያስፈልግ የኢንቨስትመንት ካፒታል በመመደብ የምርምር መሰረተ ልማት እና የሰው ሃይል ማፈላለግ በዚህ ፕሮግራም የሚከናወን ይሆናል።

**የአምራች ኢንዱስትሪ የኤክስፖርት ምርት ስብጥር እና የስትራቴጂክ ተኪ ምርቶች ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ፦** የውጤት ተኮር ማበረታቻ፣ የስትራቴጂክ የሀገር ውስጥ ተኪ ምርት ማሳደግ እና የኤክስፖርት ምርቶች ስብጥር ማስፋፋት በዚህ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። የውጤት ተኮር ማበረታቻ ፕሮግራም ለመዘርጋት የአምራች ኦንደስትሪውን አፈፃፀም ከማበረታቻ ስርዓት ጋር ያስተሳሰረ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ እና አሰራር ስርኣትን ለመዘርጋት የፋይናንስ አቅርቦት የሲስተም ዝርጋታ እና የሰው ሃይል ምደባ ተግባራትን ያካትታል። የስትራቴጂክ የሀገር ውስጥ ተኪ ምርቶችን ማሳደግ ፕሮግራም የተለዩ የስትራቴጂክ ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ የሃገር ውስጥ አምራቾች በመለየት ፋልጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ የገንዘብ፤ የአሰራር፤ እና የአጠቃላይ የድጋፍ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ማቅረብ፣ በተለዩ የስትራቴጂክ ተኪ ምርቶች ላይ ሊሰማሩ የሚችሉ አዳዲስ ባለሃብቶችን በመለየት እና በመሳብ በተናጥል ወይም በጋራ ከመንግስት ጋር ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማመቻቸት ሌላኛው የፕሮግራሙ ትኩረት ይሆናል። የኤክስፖርት ምርቶች ስብጥር ማስፋፋያ ፕሮግራም፡ የኤክስፖርት ምርቶችን አይነት፤ መጠን እና የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋፋት ዋንኛ የዚህ ፕሮግራም አላማ ሲሆን ይህንንም ለመተግበር ጥራት ያለው ባለሃብት መለየት እና ወደ ሃገር መሳብ የፕሮግራሙ አንዱ ተግባር ይሆናል።

**ዘላቂ የማኑፋክቸሪንግ ስርዓት ለመዘርጋት፦** ዘላቂና አረንጓዴ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። ይህ ፕሮግራም አምራች ኢንዱስትሪውን የሚመጥን ሰርኩላር የአመራረት እና የምርት አቅርቦት ስርዓት በመዘርጋት የአማቂ ጋዞች ልቀት መቀነስ የዚህ ፕሮግራም ትኩረት መስክ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የፋይናንስ፤ የመሰረተ ልማት እና የተቋማት አቅም ግንባታ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው። በተጨማሪም የሴት ባለሃብቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲሁም የአሰሪ ሰራተኛ ግንኙነት ምርታማነት ላይ ያተኮረ የአሰራር ስራት ለመዘርጋት የኢንቨስትመንት፤ የግብዓት አቅርቦት እና የአቅም ግንባታ ንኡስ ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና መተግበር ሌላኛው የዚህ ፕሮግራም የትኩረት መስኮች ናቸው።

### 7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲው አተገባበር ዘርፉ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ከማረጋገጥ አንጻር፣ በምርት ሰንሰለቱ ላይ አግባብነት ያለውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የግብዓት ብክነትንና ወጪን ከመቀነስ አንጻር፣ በኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር በማቀላጠፍና በማጥበቅ በምርት ሰንሰለቱ ላይ ምርታማነትን ከጥራት ጋር በማዋሃድ ተወዳዳሪነትን በጠንካራ መሠረት ላይ ከመጣል እና መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣት አንጻሁም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ከሚያደርገው አስተዋጽኦ አኳያ ስላገኘው ውጤት በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል። የክትትልና ድጋፍ ሥራው ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ የማስፈፀሚያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ይህም የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች ለማሳካትና መሳካታቸውንና ወቅታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የፖሊሲ ክለሳ ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ለማረጋገጥ ያስችላል። በአጠቃላይ ይህን የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ለመተግበር የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የፓሊሲ ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ በሚዘጋጁ ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃፊላዎች በየጊዜው የቅርብ ክትትል እየተደረገ፤ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንዲዘጋጅ ተደርጎ ይገመገማል።

- የዲጂታል የመረጃ ማሰባሰቢያ ስርዕት በመዘርጋት እና መረጃ በመሰብሰብ፣ የአፈፃፀም ሂደትን በመፈተሽ፣ አፈፃፀምን ከተቋም ዕቅድ ጋር በማነፃፀር በፓሊሲው የተቀመጡ የልማት ፕሮግራሞች ትግበራ በሚፈለገው ደረጃና ሁኔታ እየተከናወኑ መሆናቸውን በመለየት በየወቅቱ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል። የልማት ፕሮግራሞች ክትትል በተቀናጀና ወጥነት ባለው አካሄድ ለመምራት እንዲያስችል በሚቀመጠው የፓሊስ እቅድ ትግበራ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በሚመለከታቸው በፌደራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች በኩል በየደረጃው የተያዙ የልማት ፕሮግራም ዋና ዋና ተግባራቶች በተቀመጠላቸው የስራ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተከታታይነት እና ወጥ በሆነ መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸው ይፈተሻል።

- በየሦስት ዓመቱ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት በመካከለኛ ዘመን ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ ሥራዎች መሻሻል በግብዓትነት እንዲውሉ ይደረጋል። ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት ባለድርሻ አካላትና ማህበረሰቦችን አካታች በሆነ መረጃ የማሰባሰብ ዘዴ እንዲሁም በተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መሠረት አድርጎ ይከናወናል።

- ፖሊሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፖሊሲ ፋይዳ ጥናት ላይ ተመሥርቶ እንዲሻሻል ይደረጋል።

## 8. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች

በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተለዩ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው።

## 8.1 የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች እና የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች

- የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለአምራች ኢንዱስትሪው ጥራቱን የጠበቀ፣በቂ፣ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ  አስተማማኝ ግብዓት በማቅረብ በአሁኑ ሰዓት የሚታየውን የግብዓት አቅርቦት እጥረትና ጥራት መቅረፍ እንዲሁም ከአምራች ኢንዱስትሪ የሚወጡ ለግብርናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በመጠቀም አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት ዋና ዋናዎቹ ከፖሊሲው የሚጠበቁ  ጉዳዮች ናቸው፡፡

- የማዕድን ፖሊሲ ለአምራች ኢንዱስትሪው ጥራቱን የጠበቀ፣በቂ፣ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ አስተማማኝ ግብዓት በማቅረብ በአሁኑ ሰዓት የሚታየውን የግብዓት አቅርቦት እጥረትና ጥራት መቅረፍ ከዚህ ፖሊሲ ይጠበቃል፡፡

- የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ፖሊሲ አምራች ኢንዱስትሪው ጥራት ያለው ምርት እንዲያመረት እገዛ ማድረግ፣የተመረቱ ምርቶች ተገቢውን ገበያ እንዲያገኙ ማድረግ በተለይም የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ ምርቶች የገበያ መዳረሻዎችን ማሳደግ እና አማራጭ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን የማያዳክም መሆኑን ማረጋገጥ፣የንግድ ድርድር በማድረግ ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከአላስላጊ ውድድር በመከላከል አቅማቸውን ማሳደግ ከፖሊሲው የሚጠበቅ ተግባራት ይሆናሉ፡፡

- የትራንስፖርትና ሎጆስቲክስ ፖሊሲ በአምራች ዘርፉ ተመርተው በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ በተለይም ምርቶች በባቡር በመማጓጓዝ አላስፈላጊ ወጪ እንዲቀንስ ማድረግ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች በተለይም በቀላሉ የሚበላሹ ምርቶችን በኮንቴነር በሚገባ አሽጎ መላክ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣ ከውጭ ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን በተገቢው መንገድ እንዲገቡ በማድረግ አላስፈላጊ የዲመሬጅ ወጪዎችን መቀነስ ከፖሊሲው የሚጠበቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡

- የኤሌክትሪክ ፖሊሲ ለአምራች ኢንዳስትሪዎች በቂና አስተማማኝ ጥራት ያለው የሀይል አቅርቦት እንዲኖር እና ኢንዱስትሪዎች ከመንግስት ከሚቀርበው ሀይል ባሻገር የራሳቸውን የሀይል አማራጭ የሚያገኙበትን አግባብ ይቀይሳል፡፡ የውሀ ልማት ፖሊሲ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የውሀ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፤ ኢንዱስትሪዎቹም በራሳቸው ውሃ የሚያወጡበት አግባብ እንዲኖር ያግዛል፡፡

## 8.2 የማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች

- የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ በስልጠና ላይ የሚገኙ የቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ክፍሎች አምራች ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሀይል ማምረት፣ሰልጣኝ ተማሪዎች በስልጠና ላይ እያሉ ተገቢውን የተግባር ልምምድ በኢንዱስትሪዎች እንዲቀስሙ ማድረግ፣ በአምራች ዘርፍ ለሚሰማሩ አስተኛና ጥቃቅን አንቀሳቃሾች ወደ ኢንዱስትሪው ሊያስገባቸው የሚያስችል ስልጠና መስጠት የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡

## 8.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ በሀገር ደረጃ የአምራች ዘርፉን ምርታማነት ብሎም ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ፣ የተላመዱትን ወደ ምርት እንዲገቡ እና በሰፊው እንዲመረቱ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ልማት ምርምርና ጥናት በማካሄድ አምራች ኢንዱስትሪዉን መደገፍ። አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች (ስታርት አፕ) ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በትብብር መስራት ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

- የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ኢንዱስትሪ ግብዓቶችና መሳሪያዎችን ደረጃዎችን በማስጠበቅ የማረጋገጥ ሚና ይኖረዋል።

## 8.4 የፍትህና የአስተዳድር ፖሊሲዎች

- የሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውጤታማነት አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ እና የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ባለሙያዎች ማበረታቻ እንዲቀረፅ በማድረግ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት መሳብ ላይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

## 9. *መሠረታዊ የቃላት ፍቺ*

**'የአምራች ኢንዱስትሪ'** ማለት የተፈጥሮ ወይም የተለወጡ ጥሬ እቃዎችን እና የምርት ውጤቶችን በማምረቻ መሳሪያዎች፣ በሰው ኃይልና ጉልበት፣ በኬሚካል፣ በፊዚካል ወይም በባዮሎጂካል ሂደት በመለወጥ፣ በመቀመር፣ በመገጣጣም ወይም በማቀናበር አዲስ ምርት የሚያስገኝ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው።

**'የማምረት አቅም'** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪው ሊያመርት ይችላል ተብሎ የተቀመጠለት ሙሉ አቅም አጠቃቀም ማለት ነው።

**'የኢንዱስትሪ ክላስተር'** ማለት በተቀራራቢ አካባቢ ተመጋጋቢ የአምራች ኢንዱስትሪ የሚሰባሰቡበት እና የግብዓት ምርት ትስስር ለመፍጠር፣ የሰው ኃይል ለመጠቀም፣ ለገበያ ተደራሽ ለመሆን እንዲሁም የቴክኖሎጂና ዕውቀት ሽግግር ለማሳለጥ በመተባበር እና በመደጋገፍ መንፈስ በመጠቀም ተወዳዳሪ ምርት የሚያመርቱበት አሰራር ነው።

**'የኢንዱስትሪ ማፕ'** ማለት በአካባቢ ልማት ፕላን ውስጥ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሚውል የመሬት/የማምረቻ ቦታ፣ የውሃና የኤሌክቲሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የመኖሪያ ቤት ልማት፣ የፍሳሽና ተረፈ ምርት አወጋገድ እንዲሁም የማኅበራዊ አገልግሎት አቅርቦት የሚመራበት የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ (ማስተር ፕላን) ማለት ነው።

**'ክህሎት'** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪ ተግባርን በአግባባቡ ለመፈፅም የሚያስችል በልምድና በሥልጠና የተገነባ ብቃት ፣ ዕውቀት፣ የኢንዱስትሪ ባህል እና የሥራ አመራር ችሎታ ነው።

**'ልዩ የኢኮኖሚ ዞን'** ማለት መንግስት ኢንዱስትሪውን ለማበረታታት በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ገድቦ የከለላቸው አካባቢዎች ሲሆኑ የተሟላ መሠረተ ልማቶችና የተሻሻሉ የመንግስት አገልግሎቶችን ከማቅረብ ባሻገር የተለያዩ የፊስካል እና ፊስካል ያልሆኑ ማበረታቻዎች የሚሰጡበት ነው።

**'ቴክኖሎጂ'** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪው ለማምረት የሚጠቀምባቸው ማሽኖች፣ የቴክኒክ ሂደቶች፣ ዘዴዎች ወይም ዕውቀቶች ነው፡፡

**'ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ'** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪው የዲጂታል፣ የኢንተርኔት እና የገመድ አልባ ቴክኖሎጂዎችን ያካትታል፡፡

**'ተወዳዳሪነት'** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪው ምርቱ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በሚፈለገው ጊዜ በዘላቂነት በማቅረብ በገበያ ውስጥ ብልጫ ያለው ተፎካካሪ ሲሆን ነው፡፡

**'የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ'** (local content) ማለት የአምራች ኢንዱስትሪ በእያንዳንዱ የእሴት ሰንሰለት ከሚፈለጉ የምርት ግብዓቶች (የሰው ኃይል፣ ሰፕላይስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት፣ ወዘተ) ከሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ እንዲጠቀሙ ለማስቻል ወይም ለማረጋገጥ በቅድሚያ የተወሰነ ምጣኔ ነው፡፡

**'ዘላቂ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት'** ማለት የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን ከመጠን ያለፈ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን (የፍሳሽና ተረፈ ምርት አወጋገድ፣ የመሬት መራቆት፣ የደን መጨፍጨን ጨምሮ) ባቀለለ እንዲሁም የሥራ ላይ ደኅንነትን ባረጋገጠ መልኩ የሚከናወን የኢንዱስትሪ ልማት ነው፡፡

**'አካታች አምራች ኢንዱስትሪ'** ማለት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ያካተተ እና እኩል ዕድሎችን እና ፍትሃዊ ስርጭትን የሰጠ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ነው፡፡

**'ስርኩላር ምርት ሥርዓት'** ማለት በዘላቂና አካታች የኢንዱስትሪ ልማት የምርትና ግብይት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም በማምረት ሂደት ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከጥሬ ዕቃ ማምረቻ እስከ ምርት ማከማቻ፣ አቅርቦት እና በመካከላቸው ያለውን እያንዳንዱን የመኀንኘ ግኑኙነት አካባቢያዊ እና ሰብአዊ ተፅእኖን ከግምት ውስጥ ማስገባትን ያካትታል፡፡

**'ፕሮግራም'** የስትራቴጂክ ፖሊሲ ዓላማዎችን እና ውጤቶችን ለማሳካት የሚነደፉ እርስ በርስ የተያያዙ ተከታታይ ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ተዛማጅ ተግባራት ናቸው፡፡

**'የፆታ አገላለፅ'** በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡